ተረቶቻችሁ

፫ኛ ክፍል

ተረቶቻችሁ

፪

የትምህርትና ፡ ሥነ ፡ ጥበብ ፡ ሚኒስቴር ፡
በሥርዓተ ፡ ትምህርትና ፡ መጻሕፍት ፡ ዝግጅት ፡
ዋና ፡ ዲፓርትመንት ፡ ተዘጋጀ ።
አዲስ ፡ አበባ ።

መብቱ በትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር የተጠበቀ ነው ።

መጀመሪያ በ፲፱፻፶፫ ዓ. ም. ታተመ ።
እንደገና በ፲፱፻፶፭ በ፲፱፻፶፮ በ፲፱፻፶፱ በ፲፱፻፷ በ፲፱፻፷፪
በ፲፱፻፷፬ በ፲፱፻፷፭ ዓ. ም. ታተመ ።

ብርሃንና ሰላም ቀ. ኃ. ሥ. ማተሚያ ቤት ታተመ ።
አዲስ ፡ አበባ ፡ ኢትዮጵያ ፡

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

ማውጫ

ገጽ

ፈሪውና ፡ ዕድሉ ፡ . . . . ፫

ስንዝሮ ፡ . . . . ፲፭

ጅራት ፡ ቆራጣ ፡ ጠጣ ፡ . . . . ፳፬

የሀብታም ፡ ልጅና ፡ የትምህርት ፡ ጥቅም ፡ . . . ፴፫

የዝንጀሮ ፡ ሠርግ ፡ . . . . ፵፯

አንድ ፡ ቅን ፡ ደኻ ፡ ሰው ፡ . . . . ፶፭

አንዲት ፡ ወሬኛ ፡ ዔሊ ፡ . . . . ፶፱

ታሪኬ ፡ ባጭሩ ፡ . . . . ፷፩

የአህያና ፡ የውሻ ፡ ጓደኝነት ፡ . . . . ፷፯

ጠጣና ፡ ተማሪ ፡ . . . . ፸፩

ሁለት ፡ ቆቆች ፡ . . . . ፸፮

አመካኝተው ፡ በሏት ፡ . . . . ፹

አንድ ፡ ዶሮና ፡ ቀበሮ ፡ . . . . ፹፪

የአንድ ፡ ፈላስፋ ፡ ምክር ፡ . . . . ፹፭

መቅድም ።

ልዩ ፡ ልዩ ፡ የምንባብ ፡ ዓይነቶች ፡ አስፈላጊ ፡ መሆናቸውን ፡ በመገንዘብ ፡ ተረቶች ፡ ተዘጋጅተዋል ። እነዚህም ፡ ተረቶች ፡ "ተረቶቻችሁ ፡ " በሚል ፡ አርእስት ፡ ተጠቅለዋል ።

ከነዚህ ፡ ተረቶች ፡ አብዛኛዎቹ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ቤተሰቦች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የተነገሩና ፡ የሚነገሩ ፡ ናቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ እዚህ ፡ በተዘጋጀበት ፡ መልክ፡ አምረውና ፡ ተጣርተው ፡ አይነገሩም ፡ ነበር፡ እንደዚሁም ፡ እንደ ፡ አሁኑ ፡ በአንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ በሥርዓት ፡ ተበጥረው ፡ በሚያጠግብ ፡ ሁኔታ ፡ አልተሰበሰቡም ፡ ነበር ።

አሁን ፡ ግን ፡ ከያሉበት ፡ ተሰብስበውና ፡ ተመዝነው ፡ በዚች ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ የሠፈሩት ፡ ተረቶች ፡ በማጫወትና ፡ በማሳቅ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ብልኀቶችንና ፡ ቁም ፡ ነገሮችን ፡ በምሳሌነት ፡ ያስተምራሉ ። ተረቶቹም ፡ የተጻፉበት ፡ አማርኛ ፡ ከልጆች ፡ ትምህርታዊ ፡ ደረጃ ፡ ጋር ፡ እንዲወዳደር ፡ ተደርጎ ፡ በመሠራቱ ፡ በአረፍተ ፡ ነገሮች ፡ ርዝመት ፤ ከብደትና ፡ ጥምዝነት ፡ ረገድ ፡

ልጆቹን ፡ አንዳችም ፡ ችግር ፡ አይገጥማቸ
ውም ። ተረቶቹ ፡ እንደቅለታቸውና ፡ እንደ፡
ክብደታቸው ፡ በቅደም ፡ ተከተል ፡ ተዘጋጅ
ተዋል ።

የዚህ ፡ ዓይነት ፡ዝግጅት ፡ የልጆችን ፡ አን
ባቢነት ፤ አስተዋይነት ፤ ተመራማሪነትና ፡ ተሽ
ቀዳዳሚነት ፡ ርምጃ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፤ ደረጃ ፡ በደ
ረጃ ፡ ይመራል ። ስለዚህ ፡ መምህራን ፡ ተማሪ
ዎች ፡ የተጠቀሱትን ፡ ትምህርቶች ፡ እንዲ
ጠቀሙባቸው ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መጠይቃን ፡
መንፈሳቸውን ፡ እየቀሰቀሱና ፡ እያሠሩ ፡
ያተጋጉአቸው ፡ ዘንድ ፡ ያስፈልጋል ። በተ
ለይ ። ልጆች ፡ በገዛራሳቸው ፡ የተረቶቹን ፡
ምንባብ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ለማግኘት ፡ እንዲ
ችሉ ፡ በልውጥውጥ ፡ ስልቶች ፡ ቢመሯ
ቸው ፡ የመጽሐፉ ፡ አገልግሎት ፡ የበለጠ ፡
እንደሚሆን ፡ ተስፋ ፡ አለን ።

ፈሪውና ፡ ዕድሉ ፤

በአንዲት ፡ ትንሽ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ባለ ጸጋ ፡ ንጉሥ ፡ ይኖር ፡ ነበር ። እርሱም ፡ አንድ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ነበረው ። ልጁም ፡ መልከ ፡ ቀና ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ምን ፡ ይሆናል ፡ በጣም ፡ ፈሪ ፡ ነበር ።

ሲፈራ ፡ ሲቸር ፡ ይህ ፡ ልጅ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ለሽርሽር ፡ ብቻውን ፡ ወደ ፡ ዱር ፡ ሄደ ። እዚያም ፡ ዛፉን ፡ ወፉን ፡ ወንዙን ፡ ተራራውን ፡ ሲያይ ፡ ሳያውቀው ፡ መሸበት። ከዚያም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ እንዳይመለስ ፡ ስለ መሸ ፡ አውሬ ፡ ይበላኛል ፡ ብሎ ፡ ፈራ ። ቤት ፡ ባገኝ ፡ ብሎ ፡ አንድ ፡ መንገድ ፡ ተከትሎ ፡ ሲሄድ ፡ ከጫካ ፡ ውስጥ ፡ የሰው ፡ ድምፅ ፡ ሰማ ። እዚያም ፡ አምስት ፡ ሌቦች ፡ በሬ ፡ ሰርቀው ፡ አርደው ፡ ሲካፈሉ ፡ አየ ። ርቦት ፡ ስለነበር ፡ ከሥጋው ፡ እንዲሰጡት ፡ ለመናቸው ። እነሱም ፡ ጨካኝ ፡ ስለነበሩ ፡ ሥጋ ፡ ቢለምናቸው ፡ ቆዳውን ፡ ሰጡት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሰጡትን ፡ ቆዳ ፡ ይዞ ፡ ከእነርሱ ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ ከሚገኝ ፡ ዛፍ ፡ ላይ፡ ሆነና ፡ በቆዳው ፡ ተጠቅልሎ ፡ ከባላና ፡ ባላ ው ፡ ላይ ፡ ግንዱን ፡ ይዞ ፡ ተቀመጠ ። ሌሊ

ትም ፡ ሲሆን ፡ ያ ፡ ቆዳ ፡ ሸቶት ፡ ጅብ ፡ መጥቶ ፡ ከዛፉ ፡ ስር ፡ ቆመ ። ልጁም ፡ በእን ቅልፍ ፡ ልቡ ፡ ሲሮጥ ፡ ስለባነነ ፡ ደንግጦ ፡ የያዘውን ፡ ዛፍ ፡ ለቀቀው ፡ ከዛፉ ፡ ላይ ፡ መሆኑም ፡ ተረስቶት ፡ ኖሮ ፡ ብድግ ፡ ብሎ ፡ ሲንጠራራ ፡ ከሥሩ ፡ ከነበረው ፡ ጅብ ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ ወደቀ ። ወዲያውም ፡ የጅቡን ፡ ማጅራት ፡ እንቅ ፡ አድርጎ ፡ ያዘ ። ጅቡም ፡ ምን፡ ወደቀብኝ ፡ ብሎ ፡ በድንጋጤ ፡ ይዞት ፡ ተፈተለከ ። ሳያቋርጥ ፡ ይዞት ፡ እየበረረ ፡ አንድ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ሲደርስ ፡ ጅቡ ፡ ልቡ ፡ ፈንድቶ ፡ ሞተ ።

ያ ፡ ፈሪ ፡ ልጅ ፡ ግን ፡ እጅቡ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ "ኡ - ኡ"- እያለ ፡ ይጮኽ ፡ ነበር ። ጩኸቱን ፡ ሰምተው ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሲያዩት ፡ ወጡ ፡ እንዲሁም ፡ የዚያ ፡ አገር ፡ ንጉሥ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ አስጠርቷ ፡ አየችው ። በውበቱና ፡ በደም ፡ ግባቱ ፡ ተማርካ ፡ አዘነ ችለት ። ወዲያውም ፡ "ምነው ፡ ወንድ ፡ ሆነህ ፡ ፈሪ ፡ ይመስል ፡ ኡ - ኡ - ትላለህ? በአገራችን ፡ ነውር ፡ ነው ። አባቴም ፡ ንጉሡ ፡ ፈሪ ፡ አይወዱም ። አሁንም ፡ ጠርተው፡ ቢጠይቁህ ፡ በአገራችን ፡ ፉከራ ፡ ነው ፡ በላ ቸው ። " አለችና ፡ አስጠነቀቀችው ።

እውነትም ፡ ንጉሡ ፡ ጠርተው ፡ ጠየቁት ። እርሱም ፡ ልክ ፡ ልጅቷ ፡ እንደነገረቻቸው ፡ መለሰላቸው ። ለንጉሡም ፡ ልጁ ፡ ይጮኽ ፡ የነበረው ፡ የጅብ ፡ ማጅራት ፡ አንቆ ፡ እንደነበረ ፡ ባለሟሎቻቸው ፡ ነገሯቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የጎበዝ ፡ ጎበዝ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ገመቱት ፤ ወዲያውም ፡ ለወይፈት፡ አስበው ፡ ያቺን ፡ መጀመሪያ ፡ ስታየው ፡ የወደደችውን ፡ ልጃቸውን ፡ ዳሩለት ።

ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በተድላና ፡ በደስታ ፡ ሁነው ፡ የሚጉላ ፡ ጊዜያቸውን ፡ እንደጨረሱ ፡ ንጉሡ ፡ አስጠሩት ። "በዚህ ፡ በአገራችን ፡ አንድ ፡ የአስቸገረን ፡ አንበሳ ፡ አለ። ብትችል ፡ ይዘህ ፡ ከነነፍሱ ፡ ካልሆነም ፡ ገድለህ ፡ ይዘህ ፡ አምጣልኝ ።" አሉት ። እርሱም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሙያ ፡ መሥራቱ ፡ ቀርቶ ፡ መስማቱ ፡ በጣም ፡ አስደነገጠው ። ሚስቱም ፡ መደንገጡን ፡ አይታ ፡ አበረታታችውና ፡ ለአባትዋ ፡ ሄዳ ፡ ያዘዙትን ፡ ለመፈጸም ፡ ፈቃደኛ ፡ መሆኑን ፡ ነገረች ።

አንበሳውን ፡ ሄዶ ፡ የሚገጥምበት ፡ ጊዜ ፡ ቀረበ ። በጣም ፡ የምትወደውና ፡ የምታስብለት ፡ ሚስቱም ፡ ለጉዞው ፡ የሚሆነውን ፡ አዘጋጀችለት ። ዝግጅቱም ፡ ልዩ ፡

ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ጠንካራ ፡ መጠጥ ፡ ነበር ፤ በሚሄድበትም ፡ ቀን ፡ ከዚህ ፡ መጠጥ ፡ ከየዓይነቱ ፡ አጠጣችውና ፡ የቀረውን ፡ ለጉዞህ ፡ ብላ ፡ ከሚቀመጥበት ፡ ፈረስ ፡ ላይ ፡ ጫነችለት ።

እርሱም ፡ መጠጡ ፡ ብርታትና ፡ ድፍረት ፡ ሰጥቶት ፡ ፈሪነቱ ፡ ሳይሰማው ፡ ወደ ፡ አንበሳው ፡ ዋሻ ፡ ሽምጥ ፡ ጋለበ ። በጉዞው ፡ ላይ ፡ ፀሐይና ፡ መጠጡ ፡ ሰውነቱን ፡ አደከመው ። እዋሻውም ፡ ዘንድ ፡ ሲደርስ ፡ ስካሩ ፡ በረታበትና ፡ ከፈረሱ ፡ ወርዶ ፡ ከዛፍ ፡ ሥር ፡ ጋደም ፡ አለ ። ፈረሱም ፡ እንደጌታው ፡ ሸክሙንና ፡ ኮርቻውን ፡ እንደያዘ ፡ ተኛና ፡ ከሜዳው ፡ ላይ ፡ ተንደባለለ ። በዚህ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ በጠርሙስ ፡ ውስጥ ፡ የነበረው ፡ መጠጥ ፡ ጠርሙሱ ፡ ተሰበረና ፡ ፈሰሰ ።

ጊዜው ፡ ቀትር ፡ ስለነበረ ፡ አንበሳው ፡ ውኃ ፡ ሊጠጣ ፡ ከዋሻው ፡ ወጣና ፡ መጣ ። ከዚያም ፡ ፈረሱና ፡ ሰክሮ ፡ የተኛውን ፡ ፈረሰኛ ፡ አየና ፡ የሞቱ ፡ ስለመሰሉት ፡ ዝም ፡ አላቸው ። ግን ፡ ውኃ ፡ ጠምቶት ፡ ስለነበረ ፡ ከፈሰሰው ፡ መጠጥ ፡ አንድ ፡ ሁለቴ ፡ ላስ ፡ ላስ ፡ ቢያደርግለት ፡ ምላሱን ፡ አኮማተረው። ሽታውም ፡ በአፍንጫው ፡ ገብቶ ፡ አዞረ

CamScanner

ውና ፡ ከፈሪው ፡ ላይ ፡ ወደቀ ። እርሱም ፡
አንበሳው ፡ መሆኑን ፡ ሳያውቅ ፡ ሰው ፡
መስሎት ፡ "እባክህ ፡ ከላዬ ፡ ላይ ፡ ተነሥ።"
እያለ ፡ ይገፋው ፡ ጀመር ።

ስካሩም ፡ በረድ ፡ ሲልለት ፡ ከተጋደ
መበት ፡ ተነሥቶ ፡ አንበሳውን ፡ ፈረሱ ፡
መስሎት ፡ ተቀምጦ ፡ ቹ-ቹ ፡ እያለ ፡ ወደ ፡
ቤቱ ፡ ጋለበው ። የኋላ ፡ ኋላ ፡ ስካሩ ፡ ሲለ
ቀው ፡ ራሱን ፡ ሲያውቅ ፡ የሚጋልበው ፡
አንበሳ ፡ መሆኑን ፡ አየ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ቁና፡
ሙሉ ፡ ፍርሃቱ ፡ መጣበትና ፡ እንደልማዱ ፡
"ኡ-ኡ" ፡ ይል ፡ ጀመር ። በሠፈሩም ፡
ቀርቦ ፡ ስለነበረ ፡ ሕዝቡ ፡ እየወጣ ፡ ቢያ
የው ፡ "ኡ-ኡ ፡" የሚለው ፡ አንበሳ ፡ ላይ ፡ ተቀ
ምጦ ፡ መሆኑን ፡ አዩና ፡ ተገረሙ ፤ ንጉሡ ፡
ግን ፡ የላኩት ፡ ጀግናው ፡ መሆኑን ፡ አው
ቀው ፡ ከአደባባይ ፡ ወጥተው ፡ በደስታ ፡
ተቀበሉት ። ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስጋናና ፡ የከበረ ፡
ሽልማትም ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ ሰጡት ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የጀግና ፡ ጀግና ፡ ተብሎ ፡
ከሚስቱ ፡ ከንጉሡ ፡ ልጅ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡
እልፍኝ ፡ ተሰጥቶት ፡ ተቀመጠ ።

ጉበዝ ፡ በአገር ፡ ሲኖር ፡ ሁሉን ፡ ለመ
ሥራት ፡ ያስመኛል ። ስለዚህ ፡ ንጉሥ ፡ ይህን ፡

ጀግና ፡ ይዘው ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ ለመው
ጋት ፡ አሰቡ ። እርሱንም ፡ አንድ ፡ ያልተ
ገራ ፡ ሰንጋ ፡ ፈረስ ፡ ሰጥተው ፡ "የጦር ፡
አበጋዝ" ፡ ብለው ፡ ሾሙት ። ግን ፡ ጥይት ፡
ከሚተኮስበት ፡ መኻል ፡ ገብቶ ፡ የጦር ፡
መሪ ፡ መሆን ፡ ቀርቶ ፡ ያን ፡ የሰጡትንም ፡
ያልተገራ ፡ ፈረስ ፡ እንኳን ፡ መገራት ፡ ሞት፡
መስሎ ፡ ታየው ። በጣምም ፡ ደነገጠ ። ፈሪ
ነቱን ፡ የምታውቀው ፡ ሚስቱ ፡ ከፈረሱ ፡
ላይ ፡ ሲወጣ ፡ ድፍረት ፡ እንዲሰማው ፡
መድኃኒት ፡ ፈልጋ ፡ አገኘችለት ። መድኃኒ
ቱን ፡ ከግራ ፡ ክንዱ ፡ ላይ ፡ አሰራለት ፡ ከፈ
ረሱ ፡ ላይ ፡ ወጣ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ፈረሱም ፡
እርሱም ፡ ኃይል ፡ ተሰማቸው ። ጦሩ ፡ ሳይ
ዘጋጅ ፡ እርሱ ፡ ብቻውን ፡ ጋልቦ ፡ ቀደመ ።
የታሰረለት ፡ መድኃኒት ፡ ከክንዱ ፡ ላይ ፡
ድንገት ፡ እፈረሱ ፡ ላይ ፡ ቢወድቅ ፡ ፍርሃቱ፡
መጣበትና ፡ ኡ-ኡታውን ፡ ቀጠለ ። ፈረ
ሱ ፡ ግን ፡ ብርታት ፡ ጨምሮ ፡ ሲሸመጥጥ ፡
ልጁ ፡ ፈርቶ ፡ ዛፉን ፡ ወርካውን ፡ በእጁ ፡
ይዞ ፡ ለመዳን ፡ አሰበ ። ግን ፡ ከፈረሱ ፡ ኃይ
ል ፡ የተነሣ ፡ ዛፉም ፡ ወርካውም ፡ ይገነደስ፡
ነበር ። ተገንድሶ ፡ እየወደቀም ፡ ሰውና ፡
ቤት ፡ ጎዳ ። የንጉሡም ፡ ጠላቶች ፡ ይህን ፡

ሊነጋጋ ፡ ሲል ፡ ባንድ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡
ብዙ ፡ ከብቶች ፡ የታጐሩበት ፡ በረት ፡ ስለ
አገኙ ፡ ልባቸው ፡ በደስታ ፡ ረካ ። ግን ፡
ለመስረቅ ፡ ስለፈሩ ፡ ስንዝሮን ፡ መርጠው ፡
"አንተ ፡ አጭር ፡ ስለሆንህ ፡ አትታይምና ፡
አንዱን ፡ በሬ ፡ ፈትተህ ፡ አምጣልን ፡" አሉ
ት ፡ ስንዝሮም ፡ እንደተባለው ፡ ከበረቱ ፡
ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ በሬውን ፡ እየ
ጐተተ ፡ አመጣ ። ወንድሞቹ ፡ አብረውት ፡
በሬውን ፡ እየነዱ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ጫካ ፡
ገቡ ። ሰው ፡ ሊያያቸው ፡ የማይችልበት
ንም ፡ ቦታ ፡ መረጡ ።

ጫካው ፡ ከመንደሩ ፡ ራቅ ፡ ያለና ፡
ውስጡም ፡ በጣም ፡ ጭር ፡ ከማለቱ ፡ የተ
ነሣ ፡ አንዳንዴ ፡ ከሚሰማው ፡ ከወፍ ፡ ጫ
ጫታ ፡ በስተቀር ፡ ሰውና ፡ አውሬ ፡ ያለበት፡
አይመስልም ፡ ነበር ።

የፀሐይ ፡ ጮራ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ባለው ፡
ተራራ ፡ ላይ ፡ ፍንጥቅ ፡ ሲል ፤ ሰባቱ ፡ ወን
ድማማቾች ፡ በሬውን ፡ አርደው ፡ ሥጋውን
ጠብሰው ፡ መብላት ፡ ጀመሩ ። ስንዝሮን ፡
ግን ፡ እናታችን ፡ አንተን ፡ ብቻ ፡ ስለምት
ወድህ ፡ እርስዋ ፡ ታብላህ ፡ እንጂ ፡ እኛ ፡
አንሰጥህም ፡ ብለው ፡ ከለከሉት ።

ስንዝሮ ፡ በብዙ ፡ ድካምና ፡ ብልሃት ፡
በሬውን ፡ ካመጣ ፡ በኋላ ፡ እንደራበው ፡
እያወቁ ፡ ወንድሞቹ ፡ ስለከለከሉት ፡ በጣ
ም ፡ ተናደደ ። ወዲያው ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡
ሲያስብ ፡ አንድ ፡ ብልኃት ፡ አገኘና ፡ ወደ ፡
ወንድሞቹ ፡ ሄዶ ፡ "እባካችሁ ፡ ፊኛውን ፡
እንኳ ፡ ስጡኝ" ፡ ብሎ ፡ ለመናቸው ፤ እነር
ሱም ፡ ምንም ፡ ሳይጠራጠሩ ፡ "እኛ ፡ ፊኛ ፡
አንበላ ፤ ውሰደው ፡ " ብለው ፡ ወረወሩለት።

ብልጡ ፡ ስንዝሮ ፡ ፊኛውን ፡ ይዞ ፡ ከእ
ነርሱ ፡ ራቅ ፡ ወዳለ ፡ ቦታ ፡ ሄደ ። እዚያም ፡
ፊኛውን ፡ ነፍቶ ፡ እያሸ ፡ አሳደገ ፡ና ፡ አር
ጩሜ ፡ ቆርጦ ፡ እዛፍ ፡ ላይ ፡ ወጣ ። ፊኛ
ውን ፡ ባርጩሜ ፡ እየገረፈ ፡ ወንድሞቹ ፡
እንዲሰሙት ፡ ድምፁን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡
"ኡ - ኡ - ኡ ፡ አረ ፡ እኔ ፡ ብቻዬን ፡ አይደ
ለም ፡ የሰረቅሁት" ፡ እያለ ፡ ይጮህ ፡ ጀመ
ር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የበሬው ፡ ባለቤት ፡ የመ
ጣባቸው ፡ መስሏቸው ፡ የስንዝሮ ፡ ወንድ
ሞች ፡ ደነገጡና ፡ ሥጋውን ፡ ትተው ፡
ሸሹ ።

ብልጡ ፡ ስንዝሮ ፡ ይኸኔ ፡ ከዛፉ ፡ ላይ ፡
ወርዶ ፡ ከተጠበሰው ፡ ሥጋ ፡ እስኪጠግብ ፡
በላና ፡ የተረፈውን ፡ ለእናቱ ፡ ለመውሰድ ፡

ፈለገ ። ግን ፡ እንዴት ፡ መውሰድ ፡ እንደሚችል ፡ ቸገረው ፤ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ሲያስብ ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ ያንድ ፡ አህያ ፡ ድምፅ ፡ ሰማ ። ወዲያውም ፡ የድምፁን ፡ አቅጣጫ ፡ ተከትሎ ፡ ሲሄድ ፡ በጀርባው ፡ ላይ ፡ መጫኛ ፡ የተጠመጠመበት ፡ አንድ ፡ ወደል ፡ አህያ ፡ ታሥሮ ፡ ሲግጥ ፡ አገኘ ፤ ባለቤቱም ፡ ራቅ ፡ ብሎ፡ እንጨት ፡ ይፈልጥ ፡ ነበር ። ስንዝሮ ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ አህያውን ፡ ፈታና ፡ ሥጋው ፡ ወደ ፡ አለበት ፡ እየነዳ ፡ ወሰደው ። ፈጥኖም ፡ ሥጋውን ፡ በቆዳው ፡ ጠቅልሎ ፡ ጫነና ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሄዶ ፡ ለእናቴ ፡ ሰጣት ።

ስንዝሮ ፡ እንዳታለላቸው ፡ ባወቁ ፡ ጊዜ ፡ ወንድሞቹ ፡ በጣም ፡ ተናደዱና ፡ ቤቱን ፡ አቃጠሉበት ። እሱ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ሳይሳቸው ፡ አመዱን ፡ በአሥር ፡ ስልቻ ፡ ሞላና በአህያ ፡ ጭኖ ፡ ወደ ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ ይጓዝ ፡ ጀመር ።

ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ሲሄድ ፡ ዋለና ፡ ሲመሽ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ከተማ ፡ ደረሰ ። ወዲያው ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ አገኘና ፡ "የመሸብኝ ፡ እንግዳ ፡ ነኝ ፤ እባካችሁ ፡ አሳድሩኝ ፡" ብሎ ፡ ለመነ ።

የቤቱ ፡ ጌታም ፡ "ሰውዬ ፡ ምንድርነህ? ፡ ከየትስ ፡ ነው ፡ የመጣኸው?" ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ።

ስንዝሮም ፡ "እኔ ፡ የዱቄት ፡ ነጋዴ ፡ ነኝ ፡ የመጣሁትም ፡ ከሩቅ ፡ አገር ፡ ነው" ፡ ብሎ ፡ መለሰ ።

ባለቤቱም ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ነበርና ፡ "ግባ፡ እዚህ ፡ ታድራለህ" ፡ ብሎ ፡ መኝታ ፡ ቤት ፡ ሰጠው ። እራትም ፡ እንዲሰጡት ፡ አሽከሮቹን ፡ አዘዘ ።

ብልጡ ፡ ስንዝሮ ፡ በጠዋት ፡ ተነሣና ፡ "የመንግሥት ፡ ያለህ ፡ ኡ - ኡ - ኡ - ዱቄቴን" ፡ እያለ ፡ ጮኸ ። ሰዎቹም ፡ ደነገጡና፡ ወደ ፡ ስንዝሮ ፡ መጡ ። "ምነው ፡ ምን ፡ ሆንህ?" አሉና ፡ ጠየቁት ።

እርሱም ፡ "ዱቄቴን ፡ ሰርቀው ፡ ስልቻዬን ፡ ባመድ ፡ ሞሉት ፤ ማን ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ አላወቅሁም ፡ ኡ - ኡ - ኡ ዱቄቴን ፡ ዱቄቴን" ፡ እያለ ፡ ደጋግሞ ፡ ጮኸ ። ባለቤቶቹ ፡ ደነገጡ ። ሀብታሙ ፡ ሰውዬም ፡ ስማቸው ፡ እንዳይጠፋ ፡ ፈርተው ፡ "ዝም ፡ በል እባክህ ፡ ዱቄትህን ፡ እንተካልሃለን ፡ አትጮህ" ፡ ብለው ፡ ለመኑት ።

ወዲያው ፡ አሥር ፡ ስልቻ ፡ ሙሉ ፡ ዱቄት ፡ ሰጡት ። ስንዝሮ ፡ ወደ ፡ እናቱ ፡ ቤት ፡ ሲደርስ ፡ ወንድሞቹ ፡ "ይህን ፡ ሁሉ፡

ዱቄት ፡ ከየት ፡ አመጣኸው?" ብለው ፡ ጠየቁት ።

እርሱም ፡ "በዚያ ፡ ባቃጠላችሁብኝ ፡ ቤት ፡ አመድ ፡ ለወጥሁት" ፡ አላቸው ።

እነርሱም ፡ እውነት ፡ መስሏቸው ፡ ቤታቸውን ፡ አቃጥለው ፡ አመዱን ፡ በአህያ ፡ ጭነው ፡ ወደ ፡ ገበያ ፡ ሄዱ ፡ እገበያም ፡ እንደደረሱ ፡ "አመድ ፡ በዱቄት ፡ የሚለውጥ"፡ እያሉ ፡ ይጮኹ ፡ ጀመር ። በገበያ ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሳቀባቸው ። ግማሹም ፡ ይሰድባቸው ፡ ነበር ። ሌሎቹም ፡ የማናቸው፡ ቂሎች ፡ እያሉ ፡ "አመድ ፡ በዱቄት ፡ የሚለውጥ" ፡ እያሉ ፡ አላገጡባቸው ።

አሁንም ፡ ስንዝሮ ፡ እንደአታለላቸው ፡ ባወቁ ፡ ጊዜ ፡ ከፊተኛው ፡ ይበልጥ ፡ ተናደዱ ። ስለዚህ ፡ "እኛም ፡ ብድራችንን ፡ እንመልስ" ፡ ብለው ፡ ተመካከሩና ፡ በረሃብ ፡ ተሰቃይቶ ፡ እንዲሞት ፡ በትንሽ ፡ አገልግል ፡ ቆሎ ፡ አስይዘው ፡ ከአንድ ፡ ትልቅ ፡ ግንድ ፡ ጋር ፡ ካሰሩት ፡ በኋላ ፡ በአቅራቢያው ፡ ወዳለው ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ ወረወሩት ።

በግንዱም ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ሲንሳፈፍ ፡ አንድ ፡ ጌታ ፡ ሰው ፡ በዚያ ፡ በኩል ፡ ሲያ

ልፍ ፡ አየውና ፡ አሽከር ፡ ልኮ ፡ ከውኃው ፡ ውስጥ ፡ አስወጥቶ ፡ አስመጣው ፡ ስንዝሮንም ፡ ባየው ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ገርሞት ፡ "አንተ ፡ ምንድር ፡ ነህ?" ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው።

ስንዝሮም ፡ "እኔ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልእክተኛ ፡ ነኝ ። የመጣሁትም ፡ ይህን ፡ አገልግል ፡ ልሰጥህ ፡ ነው ፡ አገልግሉንም ፡ ልክ ፡ የዛሬ ፡ ወር ፡ በዚህ ፡ ሰዓት ፡ ብትከፍተው ፡ ወርቅ ፡ ሞልቶ ፡ ታገኘዋለህ ። ግን ወደ ፡ መጣሁበት ፡ ቦታ ፡ የምመለስበት ፡ ፈረስ ፡ እንድትሰጠኝ ፡ እፈልጋለሁ" ፡ አለው ።

ሀብታሙም ፡ ሰውዬ ፡ በዚህ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ተገረመ ። ደስም ፡ ብሎት ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግነና ፡ ለስንዝሮ ፡ ሠላሳ ፡ ብር ፡ ሰጥቶት ፡ በፈረስ ፡ አስቀምጦ ፡ ሸኘው ።

ስንዝሮ ፡ ባደረገው ፡ ነገር ፡ እየተደሰተ ፡ ወደቤቱ ፡ ገሠገሠ ። ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ የሚስማማበትን ፡ ዘዴ ፡ ሲያወጣና ፡ ሲያወርድ ፡ ቆይቶ ፡ አንድ ፡ ብልኃት ፡ አገኘ ። ከቤት ፡ ሲደርስ ፡ ወንድሞቹ ፡ ደነገጡና ፡ በመደነቅ ፡ "አንተ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ ጥለንህ ፡ አልነበረም ፡ እንዴ ? ከባሕር ፡ ውስጥ ፡ እንዴት

ጠጣህና ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ፈረስ ፡ ይዘህ ፡
መጣህ?” ብለው ፡ ጠየቁት ። እርሱም ፡
“መቼ ፡ ይኸ ፡ ብቻ ፡ ለናንተም ፡
ብር ፡ ይገፋላችኋለሁ” ፡ አለና ፡ ሠላሳውን ፡
ብር ፡ እፊታቸው ፡ ዘረገፈው ። ሰባቱም ፡
ሞኞች ፡ ብሩን ፡ ሲሻሙ ፡ ጥቂቶቹ ፡ ብዙ ፡
ሲወስዱ ፡ አንዳንዶቹም ፡ ጥቂት ፡ ሲያገኙ ፡
ሁለቱ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ አጡ ።

እኩል ፡ ለመከፋፈል ፡ ካለመስማማታ
ቸው ፡ የተነሣ ፡ ሰባቱም ፡ ወንድማማቾች ፡
ተጣልተው ፡ ተቀያየሙ ። ከዚያን ፡ ጊዜ ፡
ጀምሮ ፡ ስንዝሮን ፡ ለማጥቃት ፡ ሊተባበሩ፡
አልቻሉም ። የእነርሱ ፡ መጣላት ፡ ለስንዝሮ
ሰላም ፡ ሆነለት ፤ በኋላም ፡ እያንዳንዳቸው ፡
ከስንዝሮ ፡ ጋር ፡ ተዋድደው ፡ ሁሉም ፡ በሰ
ላም ፡ ይኖሩ ፡ ጀመር ።

ጅራተ ፡ ቆራጣ ፡ ጦጣ ።

ወደ ፡ አንዲት ፡ ንግሥት ፡ ከተማ ፡ በሚወ
ስድ ፡ መንገድ ፡ ዳር ፡ ባለው ፡ ጫካ ፡ ውስጥ፡
አንዲት ፡ ጅራተ ፡ ቆራጣ ፡ ጦጣ ፡ ነበረች ።
ገባሮች ፡ የአሥራት ፡ ማር ፡ በብረት ፡ ገንቦ፡

ተሸክመው ፡ ወደ ፡ ንግሥቲቱ ፡ ሲወስዱ ፡
ጦጣዋን ፡ ከመንገድ ፡ አገኙአት ። እነርሱም ፡
ከመንገዱ ፡ መርዘም ፡ የተነሣ ፡ ፀሐይ ፡ ጎድ
ቷቸው ፡ ውኃ ፡ ጠምቷቸው ፡ ነበር ። ጦጢ
ትን ፡ መንደር ፡ ወዴት ፡ እንዳለ ፡ ጠየቋት ፡
እርስዋም ፡ “በዚህ ፡ ውረዱ” ፡ ብላ ፡ የቁልቁ
ለት ፡ መንገድ ፡ መራቻቸው ። እነርሱም ፡
“በዚህ ፡ ቁልቁለት ፡ ከነገንቦአችን ፡ ለመ
ውረድ ፡ አንችልም ፡” ፡ አሉ ። በዚህ ፡ ጊዜ፡
“ምን ፡ አለ ፡ እዚህ ፡ ተውትና ፡ ሂዳችሁ ፡
ጠጥታችሁ ፡ ኑ ፡ እኔ ፡ ስጠብቅላችሁ ፡ እቆ
ያለሁ” ፡ አለቻቸው ። ሁለት ፡ ገንቦ ፡ ማር ፡
አደራ ፡ ብለው ፡ ሰጥተዋት ፡ ውኃ ፡ ጥማቸ
ውን ፡ ሊያረኩ ፡ ሄዱ ። እንኰዬ ፡ ጦጢት ፡
ግን ፡ ወዲያው ፡ ከፊቷ ፡ ራቅ ፡ ሲሉ ፡ የአን
ደኛውን ፡ ገንቦ ፡ ምርጊት ፡ ከፍታ ፡ ማሩን ፡
በጥፍሯ ፡ እየዛቀች ፡ ትልስ ፡ ጀመር ። እን
ዲህ ፡ አድርጋ ፡ ሆድዋ ፡ የቻለውን ፡ ያህል ፡
በላች ። ያጎደለችውንም ፡ ገንቦ ፡ ጭቃ ፡
ሞልታ ፡ እንደነበር ፡ አድርጋ ፡ አስቀምጣ ፡
ቆየቻቸው ።

ገባሮቹም ፡ ሲመለሱ ፡ ስለጠበቀችላቸ
ውና ፡ መንገድም ፡ ስለአሳየቻቸው ፡ አመስ
ግነው ፡ ጉዞ ፡ ቀጠሉ ። ቶሎ ፡ ቶሎም ፡ ተራ

ምደው ፡ ከንግሥቲቱ ፡ ቤተ ፡ ርስት ፡ ደር
ሰው ፡ አድረው ፡ ለንግሥቲቱ ፡ ማሩን ፡ አቀ
ረቡ ፤ ንግሥቲቱም ፡ አንደኛውን ፡ ገንቦ ፡
ብትከፍተው ፡ ቀይ ፡ መረሬ ፡ ጭቃ ፡ ሆኖ ፡
አገኘችው ። በዚህ ፡ ተደንቃ ፡ ተቆጣቻ
ቸው ። እነርሱም ፡ ደነገጡ ፡ ማር ፡ የነበ
ረው ፡ ጭቃ ፡ ስለሆነባቸው ። በኋላ ፡ ቢያ
ስቡ ፡ ጦጣይቱ ፡ እንዳታለለቻቸው ፡ ተረ
ዱት ። ለንግሥቲቱም ፡ ነገሩን ፡ ገልጸው ፡
አስረዱአት ።

ንግሥቲቱም ፡ ጦጣ ፡ እንዴት ፡ ሰውን ፡
ደፍራ ፡ ታታልላለች ፡ ብላ ፡ ተገረመች ።
በተለይም ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ዕቃ ፡ ደፍራ፡
በማጥፋቷ ፡ ተቆጣች ። ስለዚህ ፡ ይህች ፡
ጦጣ ፡ ተፈልጋ ፡ እንድትያዝ ፡ ትእዛዝ ፡
ሰጠች ። ፈላጊዎችም ፡ እንዳይቸገሩ ፡ "ምን
ምልክት ፡ አላት?" ፡ ብላ ፡ ጠየቀች ። ገባሮ
ቹም ፡ "ጅራቷ ፡ ቆራጣ ፡ ነው" ፡ አሉ ።
በዚህን ፡ ጊዜ ፡ እርስዋ ፡ ለይቶ ፡ ለመፈለግ ፡
ሁሉንም ፡ ጦጣ ፡ እንዲሰበሰቡ ፡ አዘዘች ።
ያቺ ፡ ጦጣ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ አስቀድማ ፡ ስለ
ሰማች ፡ ለጦጣዎቹ ፡ ሁሉ ፡ እየዞረች ፡ "ጅራ
ቱን ፡ ያልተቆረጠ ፡ ጦጣ ፡ ነገ ፡ ማለዳ ፡ እየ
ተያዘ ፡ ይገደላል" ፡ አለቻቸው ። ጦጣዎ

ችም ፡ የእርስዋ ፡ ጅራት ፡ መቆረጥ ፡ አይ
ተው ፡ አመኑና ፡ አንዱ ፡ አንዱን ፡ ባልተወ
ለደ ፡ አንጀቱ ፡ ጭራውን ፡ ቆረጠው ። አብ
ዛኞቹንም ፡ እርስዋ ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ እየዞረች ፡
ጎምዳ ፡ ጎምዳ ፡ ለቀቀቻቸው ።

ጠዋት ፡ ጦጣ ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስቦ ፡ ቢታ
ይ ፡ ሁሉም ፡ ጅራቱ ፡ የተቆረጠ ፡ ሆኖ ፡
ተገኘ ። እንግዲህ ፡ የትኛዋ ፡ እንደሆነች ፡
ይታወቅ ? በኋላ ፡ ዘዴ ፡ ተፈለገና ፡ ተገኘ ።
ይኸውም ፡ የበላና ፡ ያልበላውን ፡ ለመለየት
ሁሉም ፡ ከአንድ ፡ ገደል ፡ አፋፍ ፡ ወደ ፡
አንደኛው ፡ እንዲዘልሉ ፡ ነበር ። ከእርስዋ ፡
በስተቀር ፡ ሁሉም ፡ ሳይፈሩ ፡ ዘለሉ ። እር
ስዋ ፡ ግን ፡ ከነጠገበው ፡ ሆዷ ፡ ለመዝለል፡
ብትሞክር ፡ መነሣትም ፡ አቃታት ። የግድዋ
ንም ፡ ብትሞክር ፡ ከገደሉ ፡ ውስጥ ፡ ወደ
ቀች ። "ምንድር ፡ ነው ? ምን ፡ ሆንሽ?"
ቢሏት ፡ "የእናቴ ፡ መቀነት ፡ አሰናከለኝ"፡
አለች ።

እነርሱም ፡ ማሩን ፡ የበላችው ፡ እርሷ ፡
መሆኗን ፡ አውቀው ፡ "አንቺ ፡ ቀጣፊ" ፡
ብለው ፡ ይዘው ፡ ወስደው ፡ ከግንድ ፡ ጋር ፡
አሥረው ፡ ዱላ ፡ ለመቁረጥ ፡ ወደ ፡ ጫካ ፡
ሄዱ ።



ጦጢት ፡ እዚያ ፡ ታሥራ ፡ የሆን ፡ ያልሁ
ነውን ፡ ውሸቷን ፡ ስትቀባጥር ፡ ነበር ።
ጅብ ፡ እግረ ፡ መንገዱን ፡ በዚያ ፡ ሲያልፍ ፡
አይቶ ፡ "ምንሆንሽ ፡ ታሰርሽ!" አላት ።
እርስዋም ፡ "የእናት ፡ የአባቴን ፡ ተዝካር ፡
አልበላም ፡ አልጠጣም ፡ ብዬ ፡" አለችው ።
እያ ፡ ጅቦም ፡ በሆዱ ፡ ነገር ፡ እያጠናምና ፡
"እኔ ፡ እበላልሻለሁ ፡" አላት ። እርስዋ ፡
"በል ፡ ና ፡ ፍታኝና ፡ አንተን ፡ እዚህ ፡
ተከኜ ፡ መብል ፡ መጠጡን ፡ ላምጣልህ ፡"
አለችው ። "እሺ" ፡ ብሎ ፡ እርስዋን ፡ ፈትቶ ፡
እርሱ ፡ ታሰረ ። ዱላ ፡ ቆረጣ ፡ የሄዱት ፡ ገባ
ሮችም ፡ ሲመለሱ ፡ ጅቡን ፡ በማየታቸው ፡
ተደንቁ ። "ምን ፡ አመጣህ" ፡ ብለውም ፡
ጠየቁት ። ጅብም ፡ "የጦጢትን ፡ እናት ፡
አባት ፡ ተዝካር ፡ ልበላ ፡" ብሎ ፡ መለሰላ
ቸው ። እነርሱም ፡ ተናድደው ፡ በቆረጡት ፡
ዱላ ፡ ወገቡንና ፡ ግጅራት ፡ ግጅራቱን ፡
አሉት ። ጅቡም ፡ "እበላለሁ ፡ እጠጣለሁ ፡"
እያለ ፡ ጮኸ ። ዱላው ፡ ስለበዛበትም ፡
ሞተ ።
ንግሥቲቱ ፡ በጣም ፡ ብልህ ፡ ነበረች ።
አሁንም ፡ ያችን ፡ እታላይ ፡ ጦጣ ፡ ማግኛ ፡
ዘዴ ፡ አመጣች ። ጦጣዎች ፡ ሁሉ ፡ እዛፍ ፡

ቅርንጫፍ ፡ ላይ ፡ እንዲሠፍሩ ፡ በኋላም ፡ ምግብ ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ እንዲጣልላቸው ፡ አዘዙች ። ለሰዎቹም ፡ እንዲህ ፡ አለቻቸው ። "አሁን ፡ በቅርብ ፡ ጅራታቸው ፡ የተቆረጠው ፡ መቆረጣቸውን ፡ ረስተው ፡ ዛፉን ፡ በጭራቸው ፡ የያዙ ፡ መስሏቸው ፡ በሁለት ፡ እጃችን ፡ ምግቡን ፡ እንቀበላለን ፡ ሲሉ ፡ ይወድቃሉ ። ያች ፡ በፊት ፡ የተቆረጠችው ፡ ግን ፡ ለምዳለችና ፡ በአንድ ፡ እጅዋ ፡ የዛፉን ፡ ቅርንጫፍ ፡ ይዛ ፡ በአንድ ፡ እጅዋ ፡ ምግቡን ፡ ትቀበላለች"፡ አለቻቸው ።

እውነትም ፡ ጦጣዋ ፡ ልክ ፡ ንግሥቲቱ ፡ እንደተናገረችው ፡ አደረገች ። ሰዎቹም ፡ በዚሁ ፡ አውቀው ፡ ያዙና ፡ ሌባዋን ፡ ጦጣ ፡ ገርፈው ፡ ለቀቋት ።

የሀብታም ፡ ልጅና ፡ የትምህርት ፡ ጥቅም ።

አንድ ፡ ትምህርት ፡ በጣም ፡ የሚጠላ ፡ የሀብታም ፡ ልጅ ፡ ነበረ ። አባቱም ፡ ባሻ ፡ እንደልቡ ፡ የታወቀና ፡ ስመጥሩ ፡ ሀብታም ፡

ሰው ፡ ነበር ። አባቱ ፡ ብዙ ፡ ሀብት ፡ ስለነበረው ፡ ለማንኛቸውም ፡ ነገር ፡ ግድ ፡ የለውም ፡ ነበር ። እርሱም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሽር ሽር ፡ ከአባቱ ፡ አሽከሮች ፡ ጋር ፡ በፈረስ ፡ ይሄድ ፡ ነበር ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ለሽርሽር ፡ ወጥቶ ፡ ሳለ ፡ አንዲት ፡ በጣም ፡ ቆንጆ ፡ ልጅ ፡ አየና ፡ ወደዳት ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሊያገባት ፡ ፈልጎ ፡ አባቱን ፡ ከልጅቷ ፡ ጋር ፡ እንዲያጋባው ፡ ጠዋትና ፡ ማታ ፡ ይጨቀጭቀው ፡ ጀመር ።

አባትየውም ፡ ልጅቷ ፡ የድኻ ፡ ልጅ ፡ መሆኗን ፡ ካረጋገጠና ፡ ካወቀ ፡ በኋላ ፡ ልጁ ፡ እንዲያገባት ፡ አልፈቀደም ፡ ዋና ፡ ምኞቱ ፡ ልጁ ፡ የሀብታም ፡ ልጅ ፡ እንዲያገባለት ፡ ነበር ።

ሀብታሙም ፡ በጣም ፡ የሚወደው ፡ ልጁ ፡ ስላስቸገረው ፡ የልጅቷን ፡ አባትና ፡ እናት ፡ መጠየቅ ፡ ግድ ፡ ሆነበት ። የልጅቷም ፡ ቤተሰቦች ፡ "እኛ ፡ ድኾች ፡ ነንና ፡ ለሀብታም ፡ ልጅ ፡ ሠርግ ፡ የሚሆን ፡ ድግስ ፡ ለመደገስ ፡ አንችልም"፡ ብለው ፡ ለሀብታሙ ፡ ሰው ፡ መልስ ፡ ሰጡት ። ከእነርሱም ፡ ይህን ፡ ዓይነት ፡ መልስ ፡ በማግኘቱ ፡

በልቡ ፡ ያሰታ ፡ ተሰምቶት ፡ ለልጇ ፡ "እም ቢ ፡ አሉኝ"፡ ብሎ ፡ ነገረው ።

የሀብታሙ ፡ ልጅ ፡ ግን ፡ ልጅቷን ፡ ከሓ ገዛ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ተደስቶ ፡ ለመኖር ፡ የሚችል ፡ አለመሰለሀ ፡ ስለአለው ፡ ለአ ባቱ ፡ መልሶ ፡ ይሆን ፡ሃሳብ፡ገልጾ፡ነገረው።

ሀብታሙም ፡ እንደገና ፡ የልጅቷን ፡ ቤተ ሰቦች "ስለድግስ ፡ ግድ ፡ የላችሁም ፡ እታሰቡ ፡ ልጃችሁን ፡ ብቻ ፡ ለልጄ ፡ እባካ ችሁን ፡ ጻፉለት"፡ ብሎ ፡ ለመናቸው ።

የልጅቷም ፡ ቤተሰቦች ፡ የሀብታሙ ፡ ልጅ ፡ ትምህርት ፡ እንደሚጎትና ፡ እንደሚ ጠላ ፡ ያውቁ ፡ ስለነበር ፡ "ልጃችን ፡ በጣም፡ የተማረች ፡ ነች ፡ እንዴት ፡ ፊደል ፡ እንኳን፡ ያልቆጠረውን ፡ ታገባለች!"።

"ይህንንም ፡ ለማለት ፡ ያስደፈረን ፡ ምናልባት ፡ ልጁ ፡ ሀብቱን ፡ የተቀማ ፡ እን ደሆነ ፡ ከተ ፡ ችግር ፡ ያጋጥመውና ፡ ከች ግሩ ፡ ለማምለጫ ፡ ዘዴ ፡ በቶሎ ፡ ፈጥሮ ፡ ለመኖን ፡ ያዳግተዋል ፡ በማለት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ይሆን ፡ በመገንዘብ ፡ እርስዎ ፡ የመ ውቢትን ፡ ጉዳይ ፡ እጄ ፡ ብለን ፡ ልንፈጽም ልዎ ፡ ፈቃደኞች ፡ ባለመሆናችን ፡ እናዝና ለን" ፡ ብለው ፡ መለሱለት ።

ሀብታሙም ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ትምህርት፡ ከሀብት ፡ መበለጡን ፡ አያውቅም ፡ ኖሮ ፡ በነገሩቸው ፡ ተደነቀ ። ደግሞ ፡ እንዲሀ ፡ ሲል ፡ በዚያው ፡ በመሐደም ፡ አለምርው ፡ "ከእጡ ፡ ከነጡ ፡ ሀብት ፡ ዱርውን ፡ ከሌ ለ ፡ ትምህርት ፡ ከየት ፡ እምጥቶ ፡ ይሰጣል!" አለ ።

ልጇም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ትምህርት ፡ ቢጠላና ፡ ቢጎቅ ፡ ልጅቷን ፡ ከመውደዱ ፡ የተነሣ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መግባት ፡ ግድ፡ ሆነበት ። በትምህርት ፡ ቤትም ፡ ሥጋጃ ፡ መሥራትን ፡ ጣገድ ፡ እናታ ፡ ተማረ ። ግን ፡ የፊደል ፡ ዘር ፡ ለይቶ ፡ ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ ትንሽ ፡ እንደቻለ ፡ ትምህርቱ ፡ በጣም ፡ ሰለቸው ።

ልጅቷንም ፡ እንዲሀ ፡ አላት ። የመጻ ሐፍ ፡ ትምህርት ፡ በጣም ፡ ችክ አለኝ ፡ ግን ፡ ሥጋጃ ፡ መሥራትን ፡ በደንብ ፡ ተም ሬአለሁ ፡ ታዲያ ፡ አሁንስ ፡ አታገቢኝምን!" ብሎ ፡ ጠየቃት ።

እርስዋ ፡ ግን ፡ "እስከ ፡ ጭረሻ ፡ ትምህ ርት ፡ ባትጀምር ፡ ይሻል ፡ ነበር ። ትምህ ርት ፡ ምክረሀ ፡ ሲያቅትህ ፡ እንዴት ፡ ብዬ ፡ አገባሃለሁ!" ፡ ብላ ፡ እያሾፈች ፡ መለሰችለት ።



እርሱም ፡ በልጅቷ ፡ ፌዝ ፡ በጣም ፡ ተናደደ ፡ ሃሳቧንም ፡ እንደተረዳ ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ኀዘን ፡ ተሰማው ። ልጅቷንም ፡ ለማግባት ፡ አለመቻሉን ፡ አወቀ ። ትምህርቱንም ፡ ለመቀጠል ፡ የማይሆንለት ፡ መሆኑን፡ ተገነዘበ ። ልጅቷን ፡ ሳያገባ ፡ መኖር ፡ የመረረ ፡ ኀዘን ፡ የሚያመጣበት ፡ መሆኑን ፡ አውቆ ፡ መንኖ ፡ ለመሄድ ፡ ቁርጥ ፡ ሃሳብ ፡ አደረገ ።

ይህም ፡ ልጅ ፡ የተመኘው ፡ ነገር ፡ ስላል ተፈጸመለትና ፡ በኑሮውም ፡ ስላልተደሰተ ፡ ወደ ፡ እማያውቀው ፡ አገር ፡ ብቻውን ፡ ኮበለለ ። ከአንድ ፡ ደን ፡ ቦታ ፡ ሲደርስ ፡ ሽፍቶች ፡ በድንገት ፡ ደርሰው ፡ ያዙት ። እነዚህም ፡ ሽፍቶች ፡ ሊገድሉት ፡ ሲማከሩ ፡ ሰማ ። እርሱም ፡ ለጊዜው ፡ አንድ ፡ ማምለጫ ፡ ዘዴ ፡ ስላገኘ ፡ “ሥጋጃ ፡ መሥራት ፡ እችላለሁና ፡ ከምትገድሉኝ ፡ ሥጋጃ ፡ እየሠራሁላችሁ ፡ እርሱን ፡ ሸጣችሁ ፡ ብታተርፉ ፡ ይሻላችኋል” ፡ አላቸው ። ሽፍቶቹም ፡ ከምንገድለው ፡ እያሠራነው ፡ ብንጠቀም ፡ ይሻላል ፡ ብለው ፡ በነገሩ ፡ ተስማሙ ። ነገር ፡ ግን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ሥጋጃ ፡ መሥራት፡ እንዳለበት ፡ አስጠነቀቁት ።

ሀብታሙም ፡ ልጅ ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡
ሥጋጃ ፡ ይሠራ ፡ ጀምር ። ከአሰባቸው ፡ ነገ
ሮች ፡ አንድም ፡ አልሟላ ፡ ስለአለው ፡ ከመ
ጠን ፡ ያለፈ ፡ ኀዘን ፡ ተሰማው ። በመጨረ
ሻም ፡ ከሽፍቶቹ ፡ እጅ ፡ አምልጦ ፡ ለመጥ
ፋት ፡ አለመቻሉን ፡ ተረዳው ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ማምለጥ ፡ የሚ
ችልበትን ፡ ዘዴ ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ ሲያሰላስል ፡
አንድ ፡ ሃሳብ ፡ መጣለት ። ይኸውም ፡ ሽፍ
ቶቹ ፡ ሁሉ ፡ ምንም ፡ ያልተማሩ ፡ በመሆና
ቸው ፡ በሚሠራው ፡ ሥጋጃ ፡ ላይ ፡ አባቱ ፡
ከሽፍቶቹ ፡ እንዲያድነው ፡ በጽሑፍ ፡ አስ
ፍሮ ፡ የመላክ ፡ ሃሳብ ፡ ነበር ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በሚሠራው ፡ ሥጋጃ ፡
ላይ ፡ "አባቴ ፡ ባሻ ፡ እንደልቡ ፡ እኔ ፡ ልጅህ፡
ጌታነህ ፡ በሽፍቶች ፡ እጅ ፡ እሠቃያለሁና ፡
አድነኝ"፡ እያለ ፡ ይጽፍ ፡ ነበር ።

ባሻ ፡ እንደልቡም ፡ ባለብዙ ፡ ወገንና ፡
አሽከር ፡ ስለነበር ፡ ሥጋጃውን ፡ ከገዙት ፡
ሰዎች ፡ አንዱ ፡ ወስዶ ፡ አበረከተለት ።
ነገሩንም ፡ ሲረዳው ፡ ንዴትና ፡ ብስጭት ፡
አድሮበት ፡ ልጁን ፡ ለማዳን ፡ ለመሄድ ፡
ተነሣ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ወገኖቹና ፡ አሽከ
ሮቹ ፡ በርከት ፡ ብለው ፡ መሣሪያና ፡ ስንቅ ፡

ይዘው ፡ ባሻ ፡ እንደልቡን ፡"አንተ ፡ ቅር ፡
እኛ ፡ እንሄዳለን"፡ ብለው ፡ ወደ ፡ አለበት ፡
አገር ፡ ጉዞአቸውን ፡ ቀጠሉ ።

እነርሱም ፡ ከብዙ ፡ ልፋትና ፡ ጭንቅ ፡
በኋላ ፡ ሽፍቶቹን ፡ ይዘው ፡ የሀብታሙን ፡
ልጅ ፡ አስፈትተው ፡ ተመለሱ ። ሽፍቶቹ
ንም ፡ አሳልፈው ፡ለመንግሥቱ፡ሰጡአቸው ።
ሀብታሙም ፡ ሰው ፡ የሚወደውን ፡ አንድ ፡
ልጁን ፡ በሕይወቱ ፡ ስላገኘው ፡ በጣም ፡
ደስ ፡ ብሎት ፡ ለወገኖቹና ፡ ለሚያውቃቸው
ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ እንዲሁም ፡ ለአሽከሮቹ ፡
ትልቅ ፡ ግብዣ ፡ አደረገ ።

የሀብታሙም ፡ ልጅ ፡ ከሽፍቶቹ ፡ እጅ ፡
እንደወጣ ፡ ከዚያች ፡ ከሚወዳት ፡ ልጅ ፡ አገ
ረድ ፡ ዘንድ ፡ ሄዶ ፡ "የትምህርት ፡ጥቅም ፡
ገብቶኛል ። በአንቺ ፡ ንዴት ፡ የተነሣ ፡ አገር፡
አቋርጬ ፡ ስሄድ ፡ ከሽፍቶች ፡ እጅ ፡ ወደ
ቅሁ ። ከዚህም ፡ አደጋ ፡ እድን ፡ ዘንድ ፡
ትምህርት ፡ በመማሬ ፡ ሽፍቶች ፡ በሚያሠ
ሩኝ ፡ ሥጋጃ ፡ ላይ ፡ ለአባቴ ፡ ጽፌ ፡ ላከሁኝ"፡
አላት ።

ልጅቷም ፡ "ስለበደልሁህ ፡ ይቅር ፡ በ
ለኝ ። ግን ፡ እኔ ፡ እሺ ፡ ብዬ ፡ ባገባህ ፡ ኖሮ፡
የትምህርትን ፡ ጥቅም ፡ ባልተገነዘብኸውም

ነበር" ። ብላ ፡ እያጽናናች ፡ አነጋገረችው ።
ልጁም ፡ ንግግሩን ፡ በመቀጠል ፡ "ይኸ
ው ፡ አሁን ፡ ቆርጬ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡
ተመልሼ ፡ መግባቴ ፡ ነው ። ትምህርቴንም፡
ስጨርስ ፡ እንደምታገቢኝ ፡ ሙሉ ፡ ተስፋ ፡
አለኝ" ። ብሎ ፡ ፍቅር ፡ በመላበት ፡ ንግግር ፡
ሃሳቡን ፡ ገለጸላት ።

እርስዋም ፡ "የትምህርትን ፡ ጥቅም ፡ ከተ
ረዳኸውስ ፡ መጨረስህ ፡ አይቀርም ። ስለ
ዚህ ፡ ከፈለግህ ፡ አሁንም ፡ ቢሆን ፡ ተጋብ
ተን ፡ ለመኖር ፡ እንችላለን" ፡ ብላ ፡ በሚያ
ስደስት ፡ አኳኋን ፡ መለሰችለት ።

በልጅቷም ፡ ንግግር ፡ የሀብታሙ ፡
ልጅ ፡ ልብ ፡ በደስታ ፡ ረካ ፤ ትምህርቱን ፡
በቶሎ ፡ ጨርሶ ፡ አብረው ፡ በደስታ ፡ እንዲ
ኖሩ ፡ ስለወደደ ፡ ትምህርቱን ፡ ተግቶ ፡
ይማር ፡ ጀመር ። እግዚአብሔርም ፡ ረድ
ቶት ፡ ትምህርቱ ፡ ቀንቶት ፡ በቶሎ ፡ ጨረ
ሰ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አባቱ ፡ ቤት ፡ ሙሉ ፡
ድግስ ፡ ደግሶ ፡ ከዚያች ፡ ከሚወዳት ፡ ልጅ ፡
ጋር ፡ አጋባውና ፡ መልካም ፡ ኑሮ ፡ ኖሩ ።

የዝንጀሮ ፡ ሠርግ ።

በዱር ፡ የሚኖሩ ፡ ዝንጀሮዎች ፡ ተሰብስበው ፡
ወደ ፡ አንድ ፡ የስንዴ ፡ ማሳ ፡ ሄዱ ። ማሳው፡
በዓይን ፡ ለማየት ፡ እስኪታክት ፡ ድረስ ፡
ሰፊ ፡ ነው ። ስንዴው ፡ በደንብ ፡ ስላፈራ ፡
ዛላው ፡ ያማረና ፡ የሚያስጐመጅ ፡ ነው ።
ግን ፡ ሰብሉን ፡ የሚጠብቅ ፡ አንድም ፡
ሰው ፡ አልነበረም ።

ስለዚህ ፡ ዝንጀሮዎቹ ፡ ያላንዳች ፡ ፍር
ሃት ፡ በማሳው ፡ ውስጥ ፡ ተመስገው ፡ ይበሉ፡
ጀመር ። ከጠገቡም ፡ በኋላ ፡ ስንዴውን ፡
እየነቀሉ ፡ ሲደባደቡ ፡ ዋሉ ። ከእነርሱ ፡
ውስጥ ፡ አንዱ ፡ ጎረምሳ ፡ ሁሉንም ፡ ስላ
ሸነፈ ፡ ሽማግሌዎቹና ፡ አሮጊቶቹ ፡ ሚስት ፡
እንፈልግለት ፡ ብለው ፡ ተማከሩ ።

ከሽማግሌዎቹ ፡ አንዱ ፡ "እዚያ ፡ ማዶ፡
ካሉት ፡ ዝንጀሮዎች ፡ ውስጥ ፡ አንዲት ፡ ቆን
ጆ ፡ ልጃገረድ ፡ አይቻለሁና ፡ እርስዋን ፡ እን
ጥለፍለት" ፡ የማለት ፡ ሐሳብ ፡ አቀረበ ።
ሌሎቹም ፡ በነገሩ ፡ ተስማሙ ። ከዚህም ፡
በኋላ ፡ ለድግስ ፡ የሚመች ፡ ቦታ ፡ ለመምረ
ጥ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡
ገቡ ። እዚያም ፡ ማንም ፡ ሊደርስበት ፡ የማ

ይችል ፡ እልም ፡ ያለ ፡ ገደል ፡ አግኝተው ፡ እወገቡ ፡ ላይ ፡ በሰፊው ፡ የተቦረቦረ ፡ ቦታ ፡ መረጡ ።

ከዚያ ፡ በኋላ ፡ የቀረውን ፡ ሥራ ፡ ዝንጀሮዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ተከፋፈሉ ። ከአሮጊቶቹ ፡ ግማሾቹ ፡ ውኃ ፡ እንዲቀዱ ፡ ግማሾቹ ፡ ቁጫጭ ፡ እንዲለቅሙ ፡ ተደረገ ። ወጣቶቹ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ደግሞ ፡ የሾላና ፡ የዱር ፡ ፍራፍሬ ፡ እንዲለቅሙ ፡ ግማሾቹ ፡ ከገደል ፡ ማር ፡ እንዲያመጡና ፡ ከሰው ፡ እርሻ ፡ እህል ፡ እየዘረፉ ፡ እንዲያግዙ ፡ ተደለደሉ ።

ዝንጀሮዎቹ ፡ ድርሻቸውን ፡ በሚገባ ፡ አኳኋን ፡ በማከናወን ፡ ለድግሱ ፡ ተፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ አምጥተው ፡ ቅልጥ ፡ ያለ ፡ ትልቅ ፡ ድግሥ ፡ አዘጋጁ ። እኩለ ፡ ቀን ፡ ሲሆን ፡ ጎረምሶቹና ፡ ጠና ፡ ጠና ፡ ያሉት ፡ ሊጠልፉ ፡ እየጨፈሩ ፡ ሄዱ ።

“የማዶ ፡ ዝንጀሮ ፡ ሴቷን ፡ ልጅ ፡ ስጡን ፤

ዘመድ ፡ ወገናሞች ፡ እንሆናለን ።

ነገር ፡ ግን ፡ ካወቅን ፡ ከሰማን ፡ እምቢ ፡ ቢታ ፤

እንጠልፋታለን ፡ ይነገር ፡ በእንቢልታ።

ጀግንነታችንን ፡ ልታውቁት ፡ ይገባል፤

በግድ ፡ ነጥቀናችሁ ፡ ልንወስዳት ፡ መጥተናል ።

ነዪ ፡ ትንቡሼ ፡ ገላ ፡ ነዪ ፡ ትንቡሼ ፡ ገላ ፤

ለኛ ፡ ልጅ ፡ ሚስት ፡ ሁኚ ፡ ትዳሩ ፡ እንዲሞላ ፤

አትፈጪ ፡ አትጋግሪ ፡ አይጠፋ ፡ እሚበላ ፤

ቆርጦ ፡ ይሰጥሻል ፡ የስንዴውን ፡ ዛላ ፡ የማሩን ፡ ወለላ ።”

እያሉ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ድምፅ ፡ እየዘፈኑ ፡ ወደ ፡ ልጅቷ ፡ ሠፈር ፡ ተጠጉ ። እዚያም ፡ እንደደረሱ ፡ የልጅቷ ፡ ቤተሰቦች ፡ ተበታትነው ፡ ፍራፍሬ ፡ ሲለቅሙ ፡ በሩቅ ፡ አዩአቸው ። የሚፈልጓትንም ፡ የዝንጀሮ ፡ ልጃገረድ ፡ ከሌሎቹ ፡ ለየት ፡ ብላ ፡ ለብቻዋ ፡ ቁማ ፡ አዩአት ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ድምፃቸው ፡ እንዳይሰማ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ መንገድ ፡ አዋቂ ፡ እየመራቸው ፡ በጫካው ፡ ውስጥ ፡ እየተሹለከለኩ ፡ ሄዱ ። ከልጅቷ ፡ አጠገብ ፡ ሲደርሱ ፡ ሁለት ፡ ወጠምሻ ፡ ጎረምሶች ፡ ተመርጠው ፡ ልጅቷን ፡ በግድ ፡ ማጅራቷን ፡ ይዘው ፡ እንዲያመጡ ፡ ተደረገ ።

የተላኩት ፡ ጎረምሶች ፡ ልጅቷን ፡ አንቀው ፡ እየጮኸች ፡ አመጡአት ። ዘመዶችዋም ፡

ጩኸቷን ፡ ሰምተው ፡ እየተሯሯጡ ፡ ተከታ
ተሏቸው ። ልጅቷን ፡ ይዘው ፡ ምንም ፡ ያህ
ል ፡ ርቀው ፡ ሳይሄዱ ፡ የልጅቷ ፡ ዘመዶች ፡
ደረሱባቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሽማግሌዎቹ ፡
የጦር ፡ አቅድ ፡ አውጥተው ፡ ሁለቱ ፡ ጎረም
ሶች ፡ ልጅቷን ፡ ይዘው ፡ ራቅ ፡ ወዳለ ፡ ቦታ፡
እንዲሄዱ ፡ ተደረገ ፤ የቀሩት ፡ ሠርገኞች ፡
በሙሉ ፡ ዱላቸውን ፡ ይዘው ፡ በልጅቷና ፡
በዘመዶችዋ ፡ መካከል ፡ ቆመው ፡ ይጠ
ባበቁ፡ ጀመር ። የልጅቷ ፡ ወገኖች፡ ብዙዎቹ፡
ባዶ ፡ እጃቸውን ፡ ሲሆኑ ፡ ጥቂቶቹ ፡ ብቻ ፡
የዛፍ ፡ ግንጣይ ፡ ይዘዋል ። ሁለቱ ፡ ወገኖች
ግብግብ ፡ ገጥመው ፡ ይደባደቡ ፡ ጀመር ።
ከልጅቷ ፡ ወገን ፡ ብዙዎቹ ፡ ቆስለው ፡ በያለ
በት ፡ ወደቁ ። የተረፉትም ፡ መሸነፋቸውን፡
አውቀው ፡ ሸሹ ። የልጁ ፡ ወገኖች ፡ የወደቁ
ትን ፡ ተሸክመው ፡ የደከሙትንም ፡ እየደ
ገፉ ፡ ወደ ፡ ድግሱ ፡ ቦታ ፡ ጉዛቸውን ፡ ቀጠ
ሉ ። የሄዱበትም ፡ ጉዳይ ፡ ስለቀናቸው ፡ በጉ
ዞአቸው ፡ ላይ ።

"የማዶ ፡ ዝንጀሮ ፡ እማይሆነውን ፤
አንስጥም ፡ አላችሁ ፡ ሴት ፡ ልጃችሁን፤
ልታስቀሯት ፡ ኖሯል ፡ ጀግና፡ ባንሆን ።
እኛስ፡ ቆርጠን፡ ነበር፡ ፊትም፡ ስንመጣ ፤

ሞት ፡ ይሻላል ፡ ብለን ፡ እሷን ፡ ከም
ናጣ ።

በማለት ፡ እየፎከሩና ፡ እያቅራሩ ፡ ይጨ
ፍሩ ፡ ነበር ። ወደ ፡ ድግሡ ፡ ሥፍራ ፡ ሲደ
ርሱ ፡ እዚያ ፡ ቀርተው ፡ የነበሩት ፡ ወንዶ
ችና ፡ ሴቶች ፡ በጭብጨባ ፡ በዘፈንና ፡ በዕ
ልልታ ፡ ተቀበሏቸው ። ወዲያውም ፡ ምግ
ብና ፡ መጠጡ ፡ በያይነቱ ፡ ቀረበላቸው ።
ሁሉም ፡ በልተው ፡ ጠጥተው ፡ ሲጠግቡ ፡
እንደገና ፡ ቅልጥ ፡ ያለ ፡ ዘፈን ፡ ይዘፈን ፡
ጀመር ። ደከሟቸው ፡ የነበሩት ፡ ሠርገኞች፡
እንኳ ፡ ተነሥተው ፡ በእስክስታ ፡ ሙሽሮ
ቹን ፡ አስደሰቷቸው ። ታለቅስ ፡ የነበረችው፡
ሙሽራ ፡ ደስ ፡ ብሏት ፡ ከሙሽራው ፡ ጋር ፡
ትሳሳቅ ፡ ጀመር ። ወንዱም ፡ ሴቱም ፡ ሕፃ
ኑም ፡ ሽማግሌውም ፡ ሁሉ ፡ ከምግብና ፡
ከመጠጥ ፡ ብዛት ፡ በደስታ ፡ ተመልቶ ፡
ይተራመስ ፡ ነበር ። አንዳንድ ፡ አሮጊቶች ፡
ከበሮ፡ ይዘው፡ እያጨበጨቡ፡ እንዲህ፡ እያሉ፡
ይዘፍኑ ፡ ነበር ።

"እናሞግሳቸው ፡ ባንድነት ፡ አብረን፤
ይመታ ፡ ከበሮ ፡ ይዘፈን ፡ ዘፈን ፤
እይዋት፡ የኛን ፡ ሎጋ ፡ ሾላ፡ መሳይዋን ፤
ደግሞ ፡ የወገቧን ፡ እዩት ፡ መቅጠኑን ፡

ተደሰት ፡ ወገኜ ፡ ተደሰች ፡ ወገኜ ፤
ከበሮውን ፡ ምቱት ፡ እልል ፡ ልበል ፡
እኔ ።
ሰምቼውም ፡ አላውቅ ፡ አይቸውም ፡
አላውቅ ፤
እንዲህ ፡ ያለ ፡ ድግስ ፡ ሁሉንም ፡ የሚ
ያስንቅ ።
እናንት ፡ ሙሽሮች ፡ በደስታ ፡ ኑሩ ፤
እንዳዲስ ፡ ጨረቃ ፡ እንደፋኖስ ፡ አብ
ሩ ።
እናንት ፡ ወገኖቼ ፡ ስሙኝ ፡ ልንገራ
ችሁ ፤
ቆንጆ ፡ ልጅ ፡ መርጣችሁ ፡ በደንብ ፡
አመጣችሁ ።
እናሞጋግሣችሁ ፡ ባንድነት ፡ አብረን፤
ይመታ ፡ ከበሮ ፡ ይዘፈን ፡ ዘፈን ።

እንዲህ ፡ በዘፈንና ፡ በጭፈራ ፡ ሲቦርቁ፡
በድንገት ፡ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ዝንጀሮ ፡ ከው
ጭ ፡ መጣና ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ድምፅ ፡ "ዝም ፡
በሉ" ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ። ወዲያው ፡ ሁሉም ፡
ዝም ፡ አሉ ። "ከሩቅ ፡ የዝንጀሮ ፡ ጩኸት ፡
የምሰማ ፡ ይመስለኛልና ፡ እስቲ ፡ አዳምጡ"
አላቸው ። ሁሉም ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ሲያዳ
ምጡ ፡ በእውነትም ፡ ከሩቅ ፡ ቦታ ፡ ድምፅ፡

ሰሙ ። እነሱም ፡ "የልጅቷ ፡ ወገኖች ፡ መሆ
ን ፡ አለባቸው" ፡ ብለው ፡ አሰቡ ። ሁሉም ፡
ወደ ፡ ውጭ ፡ ወጥተው ፡ አተኩረው ፡ ቢመ
ለከቱ ፡ ድምፃቸው ፡ የተሰማውን፡ ፡ ዝንጀ
ሮዎች ፡ ማየት ፡ አቃታቸው ።

ባጠገባቸው ፡ ዛፍ ፡ ስለሌለ ፡ ከመካከላ
ቸው ፡ አንዱ ፡ ዝንጀሮ ፡ ብልኃት ፡ ለማግ
ኘት ፡ ጥቂት ፡ ከአሰበ ፡ በኋላ ፡ ዝንጀ
ሮዎቹን ፡ ሁሉ ፡ ጠርቶ ፡ "አንዱ ፡ በአንዱ ፡
ላይ ፡ ተነባብረን ፡ ከገደሉ ፡ ዳር ፡ ብንሆን ፡
ከላይ ፡ ያለው ፡ የጠላቶቻችን ፡ አመጣጥ ፡
ሊለይ ፡ ይችላል" ። አላቸው ። ሁሉም ፡ በነ
ገሩ ፡ ተስማምተው ፡ የሽማግሌውን ፡ ሐሳብ፡
ተቀበሉ ። መጀመሪያ ፡ ጠንካራና ፡ ግዙፍ ፡
የሆነ ፡ ስለተፈለገ ፡ ወንዱ ፡ ሙሽራ ፡ ከሥ
ር ፡ እንዲሆን ፡ ተደረገ ።

ሙሽራዪቱን ፡ የሚጠብቁ ፡ ጥቂት ፡ አሮ
ጊቶችና ፡ ሕፃናት ፡ ሲቀሩ ፡ ሌሎቹ ፡ በሙሉ
አንዱ ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ ተነባብረው ፡ አንድ ፡
ረዥም ፡ ዛፍ ፡ አከሉ ። አሁን ፡ ከላይ ፡ ያለ
ው ፡ ዝንጀሮ ፡ ጠላቶች ፡ ያሉበትን ፡ ሲመለ
ከት ፡ ሙሽራዪቱን ፡ አንዲት ፡ ንብ ፡ ጆሮ
ዋን ፡ ነድፋት ፡ ኖሮ ፡ "ውይ ፡ እማምዬ" ፡
ብላ ፡ በኃይል ፡ ጮኸች ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡

በሥር ፡ ሆኖ ፡ ሁሉንም ፡ ይዞ ፡ የነበረው ፡ ወንዱ ፡ ሙሽራ ፡ "ወይኔ ፡ ሚስቴን" ፡ አለና ፡ ከሥር ፡ ሾልኮ ፡ ወደ ፡ ሙሽራዪቱ ፡ ሲሮጥ ፡ ተነባብረው ፡ የነበሩት ፡ ዝንጀሮ ዎች ፡ ሁሉ ፡ ተንከባልለው ፡ ከገደል ፡ ገቡና ፡ አለቁ ።

አንድ ፡ ቅን ፡ ድኻ ፡ ሰው ።

በጣም ፡ ችግረኛ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበር ። እርሱም ፡ የዕለት ፡ ምግብ ፡ እንኳ ፡ ስለሌለው ፡ እንጨት ፡ እየሸጠ ፡ ምሳና ፡ ራቱን ፡ ይበላ ፡ ነበር ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እንደልማዱ ፡ መጥረቢያውን ፡ ይዞ ፡ እንጨት ፡ ለመፍ ለጥ ፡ ወደ ፡ ጫካ ፡ ሄደ ። በጫካውም ፡ ውስ ጥ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ሐይቅ ፡ ነበር ። በሐይ ቁም ፡ አጠገብ ፡ አንድ ፡ በቁሙ ፡ የደረቀ ፡ ዛፍ ፡ ስለ ፡ አየ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አለው ። ደህና ፡ ዋጋም ፡ እንደሚያወጣለት ፡ ተስፋ ፡ አድርጎ ፡ መጥረቢያውን ፡ ይዞ ፡ ከዛፉ ፡ ላይ ፡ ወጣና ፡ ቅርንጫፎቹን ፡ ይቆርጥ ፡ ጀመር ።

መጥረቢያውን ፡ ከትከሻው ፡ ላይ ፡ አድ
ርጎ ፡ የቆረጠውን ፡ እንጨት ፡ ለማውረድ ፡
ሲል ፡ ቅርንጫፉ ፡ መጥረቢያውን ፡ ከትከ
ሻው ፡ ላይ ፡ ሐይቁ ፡ ውስጥ ፡ ጣለበት ።
ድኻውም ፡ ሰው ፡ በጣም ፡ ደነገጠ ። "ቀኝ ፡
እጂ ፡ ተቆርጦ ፡ ወደቀብኝ ፤ አንድ ፡ ዓይኔም
ፈሰሰ ፤ እጄም ፡ እግሬም ፡ ዓይኔም ፡ መጥረ
ቢያዬ ፡ ነበረ ። እንግዲህ ፡ እኔም ፡ መሞቴ ፡
ነው ። ልጆቼም ፡ በችጋር ፡ ማለቃቸው ፡
ነው ። አሁን ፡ እንጨቱን ፡ በምን ፡ እፈልጠ
ዋለሁ ፡ ሌላ ፡ መጥረቢያ ፡ እንዳልገዛ ፡ ገን
ዘብ ፡ የለኝ ፡ ለራቴ ፡ መግዣ ፡ እንኳ ፡ አልያ
ዝኩም ። በመከራ ፡ ላይ ፡ መከራ ፤ በኀዘን ፡
ላይ፡ኀዘን፡ተጨመረብኝ"፡እያለ፡ያዝን፡ጀመር።

እንደዚህም ፡ ባለ ፡ እኳኋን ፡ ከዛፉ ፡
ላይ ፡ ሆኖ ፡ እንገቱን ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ አቀር
ቅሮ ፡ ሲያለቅስ ፡ ከበላዩ ፡ ድምፅ ፡ ሰማ ።
ቀና ፡ ብሎም ፡ ቢመለከት ፡ አንድ ፡ መል
አክ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ሲመጣ ፡ አየ ።

መልአኩም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ተጠግቶ ፡
"ምን ፡ ሆነህ ፡ ታለቅሳለህ?" አለው ። እር
ሱም ፡ "የዕለት ፡ ምግቤን ፡ የሚያበላኝ ፡
መጥረቢያዬ ፡ ከዚህ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ ወደ
ቀብኝ ። ማውጣት ፡ ስለ ፡ አልቻልሁ ፡ መሪ

ር ፡ ኀዘን ፡ ተሰምቶኛ ፡ ነው ፡ የማለቅሰው”፡ ብሎ ፡ በሚያሳዝን ፡ አነጋገር ፡ መለሰለት ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ መልአኩ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ ጠለቀና ፡ አንድ ፡ የወርቅ ፡ መጥረቢያ ፡ አውጥቶ ፡ ቢሰጠው ፡ “ይህ ፡ የኔ ፡ አይደለም”፡ አለው ። መልአኩም ፡ እንደገና ፡ ጠለቀና ፡ የብር ፡ መጥረቢያ ፡ አውጥቶ ፡ ቢሰጠው ፤ “ይህም ፡ የኔ ፡ አይደለም” ፡ አለው ።

አሁንም ፡ ደግሞ ፡ ሦስተኛ ፡ ጊዜ ፡ ጠለቀና ፡ የራሱን ፡ መጥረቢያ ፡ አውጥቶ ፡ ቢሰጠው ፡ ሰውየውም ፡ እግዚአብሔርንና ፡ መልአኩን ፡ እያመሰገነ ፡ በደስታ ፡ ወደ ፡ ሥራው ፡ ተመለሰ ። በርከት ፡ ያለ ፡ እንጨትም ፡ ቆረጠ ።

የቆረጠውንም ፡ እንጨት ፡ ወደገበያ ፡ ወስዶ ፡ በደህና ፡ ዋጋ ፡ ሸጠው ። እንደገናም ወደ ፡ ጫካው ፡ ሄዶ ፡ ብዙ ፡ እንጨት ፡ ቆርጦ ፡ ሸጠ ። እንዲሁም ፡ እያደረገ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ኖረ ። እንጨቱንም ፡ ወደ ፡ ገበያ ፡ ሲወስደው ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ ይሸጥለት ፡ ጀመር ። በርከት ፡ ያለ ፡ ገንዘብም ፡ አጠራቀመ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንጨት ፡ መሸጡን ፡ ትቶ ፡ ራቅ ፡ ወዳሉ ፡ አገሮች ፡ እየሄደ ፡ ፍየሎችና ፡ በጎች ፡ እያመጣ ፡ ይሸጥ ፡ ጀመር ።

ከፊተኛው ፡ የበለጠ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አገኘ፡ የፍየልና ፡ የበግ ፡ ነጋዴም ፡ ሆኖ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ እንደሠራ ፡ ብዙ ፡ ሀብት ፡ አግኝቶ ፡ የከብት ፡ ነጋዴ ፡ ሆነ ። ከአገር ፡ ወደ ፡ አገር እየዞረ ፡ ብዙ ፡ ከብት ፡ እየገዛ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ዋጋ ፡ መሸጥ ፡ ጀመረ ።

ይህም ፡ ሰው ፡ ከድህነት ፡ ወጥቶ ፡ ጠንክሮ ፡ በቅን ፡ ልቦናው ፡ እየሠራ ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ባለጸጋ ፡ ሆኖ ፡ በተድላና ፡ በደስታ ፡ ቤተሰቦቹን ፡ እያስተዳደረ ፡ ይኖር ፡ ጀመር።

አንዲት ፡ ወሬኛ ፡ ዔሊ ።

ከብዙ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ በአንድ ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ አንዲት ፡ ዔሊ ፡ ትኖር ፡ ነበር ። በሸለቆውም ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ምንጭ ፡ ነበር ። ዔሊዋ ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ወሬኛ ፡ ነበረች ። ሴቶች ፡ ውኃ ፡ ለመቅዳት ፡ ሲሄዱ ፡ ብዙ ፡ ወሬ ፡ እያወራችላቸው ፡ ሥራ ፡ ታስፈታቸው ፡ ነበር ።

የምታወራላቸውም ፡ ወሬ ፡ አብዛኛውን፡ ድንጋይ ፡ ስለመልበስዋና ፡ ስለ ፡ ጥንት ፡ ተረቶች ፡ ነበር ።

ከጨለማ ቤትዋ፡እንድ፡ቀን፡እንደ ልማድዋ፡ለማ
ውራት፡ሴቶች፡ውኃ፡ሲቀዱ፡መጥተው፡
እንደሁ፡ለማየት፡ቀና፡ብላ፡ብትመለከት
ሁለት፡ አሞራዎች፡ ተቀምጠው፡ ሲያ
ውሩ፡አየች፡ወዲያው፡ወደ፡አሞሮቹ፡
ሄዳ፡"እንደምን፡ሰንብታችኋል!" ብላ፡ሰላ
ምታ፡አቀረበችላቸው።

እነርሱም፡"እግዚአብሔር፡ ይመስገን፡
ደህና፡ነን"፡ብለው፡ለሰላምታዋ፡መልስ
ሰጡአት።

ወዲያው፡ የተለመደ፡ ወሬዋን፡ ጀመ
ረች፡ "መቼስ፡እንደናንተ፡ የታደለ፡ የለ
ም፡ምክንያቱም፡በሰማይ፡ስትበሩ፡ብዙ፡
ነገር፡ ታያላችሁ። ከአንድ፡ ቦታ፡ ወደ፡
አንድ፡ቦታ፡በቶሎ፡ለመድረስ፡ትችላላ
ችሁ። ጠላቶቻችሁ፡ ብዙ፡ አይደሉም፡
ብዙ፡ሊያጠቁችሁ፡አይችሉም"፡አለቻቸው።

አሞራዎች፤"አዎን፡ብዙ፡ነገር፡እና
ያለን። ከፈለግንበትም፡ቦታ፡በቶሎ፡እንደ
ርሳለን። እንዳንችም፡ብዙ፡ጠላቶች፡የሉ
ንም"፡እያሉ፡ሐሳብዋን፡ደገፉላት።

ጥሩ፡አጋጣሚ፡አገኘሁ፡ብላ፡ዔሊ.ዋ፡ደስ፡
እያላት፡ወሬዋን፡ቀጠለች። "በእውነቱ፡
ከዚ፡ይልቅ፡የሞተ፡ይሻላል፡ወደ፡አንድ

ቦታ፡ዘመድ፡ለመጠየቅ፡ስሄድ፡ልጆች፡
ያገኙኝ፡ እንደሆን፡ እያገላበጡና፡ እየረጋ
ገጡ፡ስቃዬን፡ያሳዩኛል። ጠላቴ፡ያገኘኝ፡
እንደሆን፡ እድንጋዬ፡ ልብስም፡ ውስጥ፡
ብደበቅ፡ እንኳ፡ አላመልጠውም። በጥ
ፍሩ፡ቧጥጦ፡ይገድለኝና፡እየቦጠቦጠ፡ይ
በላኛል"፡አለቻቸው።

አሞራዎች፤ችግሯን፡አስተውለው፡
ስለአዘኑላት፡"ምን፡እናድርግልሽ?" ብለ
ው፡ጠየቋት። እስዋም፡"ይህችን፡ዓለም፡
ለአንድ፡አፍታ፡እንኳ፡ለማየት፡ብዙ፡
ጊዜ፡እመኛለሁ። እስቲ፡እባካችሁ፡ለጥ
ቂት፡ጊዜ፡እንኳ፡ተሸክማችሁ፡አዙሩኝ"፣
ብላ፡ለመነቻቸው። አሞራዎች፤"እሺ፡
ምን፡ከፋን"፡አሉና፡ከእነርሱ፡አንዱ፡
ወደ፡ሜካ፡ሂዶ፡አንድ፡ጠንካራ፡ሐረግ፡
አመጣና፡"በይ፡ይህን፡ሐረግ፡እመሐሉ፡
ላይ፡በጥርስሽ፡ነክሰሽ፡ያዢ፡እኛ፡ጫፉ
ን፡ይዘን፡ስንበር፡አንቺ፡የምትፈልጊ
ውን፡ሁሉ፡ማየት፡ትችያለሽ። ግን፡አን
ድ፡ቃል፡እንኳ፡ለመናገር፡እንዳትሞክሪ፡
ብትናገሪ፡ወድቀሽ፡ትሞቻለሽ"፡ብለው፡
አስጠነቀቋትና፡ጉዞአቸውን፡ጀመሩ።

አሞሮቹ፡ወደ፡ሰማይ፡እየራቁ፡ወጡ፡

ዔሊዋ ፡ ከጫፍ ፡ በላይ ፡ ሆነች ፡፡ ሦስቱም ፡ ምንም ፡ ሳይነጋገሩ ፡ ሜዳውን ፡ አቋርጠው፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ሸለቆ ፡ ደረሱ ፡፡ እርሱንም ፡ በፍጥነት ፡ አቋርጠው ፡ ጥቅጥቅ ፡ ያለ ፡ ጫካ ፡ ያለበት ፡ ተራራ ፡ አገኙ ፡፡ ያንንም ፡ እየዞሩ ፡ ለዔሊዋ ፡ ካሳዩ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ መንደር ፡ ሄደው ፡ በቤቶቹ ፡ ላይ ፡ እያንዣበቡ ፡ ሕዝቡን ፡ አሳዩአት ፡ ዔሊዋ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ደስ ፡ አላት ፡፡ በተለይም ፡ የምታውቃቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁኔታዋን ፡ ተመልክተው ፡ ሲያደንቁ ፡ በማየቷ ፡ ኩራት ፡ ተሰማት ፡፡

የመንደሩ ፡ ልጆች ፡ ዔሊዋን ፡ በአየር ፡ ላይ ፡ ተመልክተው ፡ እየማቁ ፡ "ዛሬስ ፡ ደህና ፡ ዔሊ ፡ ብላ ፡ ብላ ፡ ከእዋሮች ፡ ጋር ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ ትበር ፡ ጀመር" ፡ ብለው ፡ ተከታተሏቸው ፡፡ አንዳንድ ፡ ልጆች ፡ "የዚ ች ፡ ዔሊ ፡ ነገር ፡ አይታመንም ፡ እሷ ፡ ለራሷ ፡ ወሬኛ ፡ ነች ፡፡ ላውራ ፡ ብላ ፡ ሐረጉን ፡ የለቀ ቀች ፡ እንደሆን ፡ መውደቋ ፡ እኮ ፡ ነው" ፡ እያሉ ፡ ሲተቹ ፡ ዔሊዋ ፡ ሰማቻቸው ፡፡ ወዲያው ፡ አላስችል ፡ ብሏት ፡ "እኔ ፡ ምኝ ፡ መስ ሎኋችሁ ፡ እንዴ!" ፡ ለማለት ፡ ፈልጋ ፡ አፏን ፡ ከፈት ፡ ስታደርግ ፡ የነከሰችውን ፡

ሐረግ ፡ ለቀቀችና ፡ እየተውዘወዘች ፡ እመረት ፡ ወድቃ ፡ ተሰባበረ ፡ ሞተች ።

ታሪኬ ፡ ባጭሩ ።

"ሰኞ ፡ ተረገዝኩ ፡ ማክሰኞ ፡ ተወለድኩ ፡ ረቡዕ ፡ ክርስትና ፡ ተነሣሁ ። ሐሙስ ፡ እንጨት ፡ ለቀማ ፡ ሄድኩኝ ።

እንጨት ፡ ለቀማ ፡ ሄጄ ፡ ግራሩን ፡ ጥዱን ፡ ወይራውን ፡ ዝግባውንና ፡ ሾላውን ፡ ብፈልጠው ፡ ዐረር ፡ ሆነብኝ ። በዚህ ፡ ተጨነቅሁ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ስል ፡ [illegible] ፡ የሆነ ፡ እንደኳሉላ ፡ አገኘሁ ፡ በመጥረቢያዬ ፡ ብተረከከው ፡ ጥሩ ፡ ፍልጥ ፡ ሆነ ።

ከዚያም ፡ ይህን ፡ ፍልጥ ፡ በገመድና ፡ በመጫኛ ፡ ለማሠር ፡ ብሞክር ፡ ገመዱና ፡ መጫኛው ፡ እየተበጠሰ ፡ አለቀ ። ጠንቀኛና ፡ ሐረግ ፡ ስፈልግ ፡ የሸረሪት ፡ ድር ፡ አገኘሁ ።

በሸረሪት ፡ ድር ፡ አሥሬ ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ለመሄድ ፡ እንጨቱን ፡ ለማንሳት ፡ ብሞክር ፡ በጣም ፡ ከበደኝ ።

ትልቅ ፡ ድንጋይ ፡ ጨምሬ ፡ ባነሣው ፡ ቀለለኝ ። ተሸክሜ ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ስሄድ ፡ ውኃ ፡ ጠማኝና ፡ ለመጠጣት ፡ ሸክሜን ፡ ከአንድ ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ አሳረፍኩት ።

እዚያም ፡ መጥረቢያየን ፡ ረስቼው ፡ ኖር ፡ ትዝ ፡ አለኝና ፡ ለማምጣት ፡ ወደ ፡ ተውኩበት ፡ ሥፍራ ፡ ሄድሁ ።

እዚያም ፡ ስደርስ ፡ ብረቱን ፡ ምስጥ ፡ እንክት ፡ አድርጎ ፡ በልቶት ፡ ዛቢያውን ፡ ብቻ ፡ አገኘሁት ። ተመልሼ ፡ እንጨቱን ፡ ተሸክሜ ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ሄድሁ ።

አቢት ፡ ስደርስ ፡ አባቴ ፡ ፍልጡን ፡ አይተው ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ስላላቸው ፡ አንድ ፡ ጊደር ፡ ሸለሙኝ ።

እኔ ፡ ጊደሪን ፡ በመሸለሜ ፡ ደስ ፡ አለኝ፡ ከረቢት ፡ ወይፈን ፡ ለምኜ ፡ አስጠቃኋት ። ጊደሯም ፡ ወዲያው ፡ ወለደችና ፡ አለብኳት። ግን ፡ ወዲያው ፡ ልጆቹን ፡ እይታ ፡ ጠፋችብኝ ።

ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ እየሮጥሁ ፡ ብፈልጋት ፡ አጣኋት ። በኋላ ፡ አንድ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ወጥቼ ፡ በመለከት ፡ ለማግኘት ፡ አልቻልኩም ። ፈጽሞም ፡ ባገር ፡ የለችም ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ትዝ ፡ አለኝ ፡ ለካስ ፡ አባቴ ፡ የውኃ ፡ ጉድጓድ ፡ ቆ

ፍረው ፡ ኖሮ ፡ ከእዚያ ፡ ውስጥ ፡ ገብቼ ፡ በወስፌ ፡ ላይ ፡ ቆሜ ፡ በመርፌ ፡ ቀዳዳ ፡ ብመለከት ፡ ጐንደር ፡ ላይ ፡ በመጫኛ ፡ ጠልፈው ፡ በካራ ፡ ሲያርዷት ፡ አየሁ ፡፡

ከዚያም ፡ ቅደም ፡ የሚባለውን ፡ ፈረሴን ፡ ጭኜ ፡ ሽምጥ ፡ ስጋልብ ፡ አንድ ፡ ገደል ፡ አፋፍ ፡ ደረስኩ ፡፡ ፈረሱም ፡ አልገታ ፡ አለና ፡ ተሰባብሮ ፡ ወደቀ ፡፡

እኔ ፡ ግን ፡ እምቢ ፡ ብዬ ፡ ኮርቻው ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ ብዬ ፡ ስጋልብ ፡ ጐንደር ፡ ደረስኩ ፡፡ ሰዎቹም ፡ ያውቁኝ ፡ ነበርና ፡ እዋጥተው ፡ ሰባት ፡ ጨፍዎች ፡ ሰጡኝ ፡፡

እነዚህን ፡ ሰባት ፡ ጨፎች ፡ በሰባት ፡ እህዮች ፡ ጭኜ ፡ ወደ ፡ አገሬ ፡ መጣሁ ፡፡ አገሬም ፡ በደረስኩ ፡ ጊዜ ፡ የአባቴ ፡ በሬ ፡ ከነገበሬው ፡ ሲጫጫህ ፡ ደረስኩ ፡፡

ጨፋንም ፡ አዘራሁና ፡ አሳጭጄ ፡ አስወቃሁና ፡ በሰላሳ ፡ አህያ ፡ ጭኜ ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ስሄድ ፡ ከየት ፡ መጣ ፡ ሳይባል ፡ ኃይለኛ ዝናብ ፡ መጣና ፡ አህዮቼን ፡ ከነጭነታቸው ፡ አራሳቸው ፡፡

ጨፋም ፡ የሚጐዳብኝ ፡ ስለሆነ ፡ ፀጉሬ፡ ትልቅ፡ነበርና፡ሠላሳዎቼን፡አህዮች፡ከዝናቡ፡ በፀጉሬ፡ጥላ፡አዳንኳቸው፡፡ ዝናቡም፡ሲያባራ፡

ጎፈሬዩ ፡ በጣም ፡ ስለከበደኝ ፡ አራገፍኩት፡፡ በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ከፀጉሬ ፡ የወረደው ፡ ውኃ ፡ ጐርፍ ፡ ሆና ፡ አህዮቼን ፡ አጥለቀለቃቸው ፡፡ እኔም ፡ እያዘንኩ ፡ ባዶ ፡ እጄን ፡ ወደ ፡ ቤቴ፡ ተመለስኩ ፡፡

ታሪኬን ፡ የሰሙ ፡ ተገረሙ ፡ ሁኔታዬን ፡ ያዩ ፡ ተደነቁ ፡ ነገሩ ፡ የገባቸው ፡ ለጉድ ፡ የፈጠረው” ፡ አሉ ፡፡

የአህያና ፡ የውሻ ፡ ጓደኝነት ፡፡

አንድ ፡ ዘመን ፡ አህያና ፡ ውሻ ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ ኑሮ ፡ ተመርረው ፡ ችግራቸውን ፡ እንደዚህ ፡ እያሉ ፡ ተወያዩ ፡፡

አህያ ፡- “እባክህ ፡ አቶ ፡ ውሻ ፡ የሰው ፡ ቤት ፡ ኑሮ ፡ በጣም ፡ አስመርሮኛል ፡፡ እንደምታየው ፡ ሥራዬ ፡ ከባድ ፡ ነው ፡፡ እህል ፡ ከውድማ ፡ በብዙ ፡ ተሸክሜ ፡ አምጥቼ ፡ ከጐተራ ፡ ከመከተቴ ፡ በላይ ፡ ከብዶኝ ፡ ትንሽ፡ ያቃስትሁ ፡ እንደሆነ ፡ በዱላ ፡ ይነርቱኛል ፡፡ ለበሬ ፡ እንኳ ፡ ሳይቀር ፡ ገለባ ፡ የምጭነው ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ስሠራ ፡ ከተጫንኩት ፡ ገለባ ፡ እንኳ ፡ እንዳል

በላ ፡ የባርሩኛል ፡ ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ የሚ
ነደኝ ፡ "ለአህያ ፡ ማር ፡ አይጥማት" ፡
ኢያሉ ፡ ሲያሾፉብኝ ፡ ነው ። ለእኔ ፡ እንኳ
ንስ ፡ ማር ፡ ሊሰጡኝና ፡ ገለባ ፡ እንኳ ፡ ተነ
ፍጌ ፡ ቀለቤ ፡ አመድ ፡ ሆኗል ። ስለዚህ፡
እንደዚህ ፡ እየተበሳጨሁ ፡ በሰው ፡ ቤት ፡
ለመኖር ፡ አልመኝምና ፡ ከአገር ፡ መጥፋቴ፡
ነው ። እንዲያውም ፡ ባስበው ፡ የአንተም ፡
ኑሮ ፡ እንደኔው ፡ ብስጭት ፡ ያለበት ፡ ሳይ
ሆን ፡ አይቀርም" ።

ውሻ ፡- "አዬ ፡ እመት ፡ አህዩት ፡ የኔማ፡
ግፍ ፡ ስንቱ ፡ ተቆጥሮ ፡ እንደምታውቂው ፡
አንድ ፡ ሌሊት ፡ ሙሉ ፡ እንቅልፍ ፡ ሳየም
ረኝ ፡ የጌታዬን ፡ ግቢ ፡ ፀጥታ ፡ ለመጠበቅ ፡
ከሌባና ፡ ከአውሬ ፡ ጋር ፡ ስታገል ፡ አድራ
ለሁ ። ቀኑንም ፡ እንደዚሁ ፡ ጌታዬን ፡ ተከ
ትዬ ፡ ወደ ፡ እርሻ ፡ ቦታ ፡ ሄጄ ፡ ከአረኞች፡
ጋር ፡ ከብት ፡ ስጠብቅ ፡ እውላለሁ ። ነገር ፡
ግን ፡ እንደ ፡ አገልግሎቴ ፡ ብዛት ፡ አንድ ፡
ቀን ፡ እንኳ ፡ ቀለቤን ፡ አግኝቼ ፡ አላውቅም፡
እነሱ ፡ ሲበሉ ፡ እየጓጓሁ ፡ የተመለከትሁ ፡
እንደሆነ ፡ በደህና ፡ ዱላ ፡ ወገቤን ፡ ብለው ፡
ነዩ ፡ ውጪ ፡ እኮ ፡ ይሉኛል ። በእኔ ፡ በኩል፡
ግን ፡ ደህና ፡ ምግብ ፡ ተዘጋጅልኝ፡የምለው፡

የእህል ፡ ንፋሽ ፡ የዕሌት ፡ ቂጣ ፡ ያገኘሁ ፡
እንደሆነ ፡ ነው ። አለበለዚያ ፡ ከወዲያ ፡
ወዲህ ፡ ተልከስክሼ ፡ ካልቃረምኩ ፡ በስተ
ቀር ፡ አስበው ፡ ለእኔ ፡ የሚያደርጉልኝ ፡
ነገር ፡ ከቶ ፡ የለም ። እንደምትዪውም ፡ እኔ
ንም ፡ 'በውሻ ፡ ሆድ ፡ ቅቤ ፡ አይደርም'፡
ኢያሉ ፡ ኢያፌዙብኝ ፡ ምርር ፡ ብሎኝ ፡ የማ
ማከረው ፡ ጓደኛ ፡ እፈልግ ፡ ነበር ። አንቺን፡
ካገኘሁስ ፡ አብረን ፡ እንጥፋ" ፡ ተባብለው፡
አብረው ፡ ጠፉ ።

ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ሲገሠግሡ ፡ ለምለም ፡
ሜዳ ፡ ላይ ፡ ሊያድሩ ፡ ተስማሙ ። ጊዜው ፡
እየጨለመ ፡ ሄደ ። አህያም ፡ ርቧት ፡ ስለ
ነበር ፡ ለምለሙን ፡ ሣር ፡ መንጨት ፡ ጀመ
ረች ፡ ውሻ ፡ ግን ፡ ለእሱ ፡ የሚሆን ፡ ምግብ፡
ስላላገኘ ፡ ጠሙን ፡ እንደዋለ ፡ ኩርምት ፡
ብሎ ፡ ተኛ ።

አህዩት ፡ እኩለ ፡ ሌሊት ፡ ድረስ ፡ ከጋ
ጠች ፡ በኋላ ፡ ጥጋብ ፡ ተሰምቷት ፡ ኖሮ ፡
አቶ ፡ ውሻን ፡ ከእንቅልፉ ፡ ቀስቅሳ ፡ "እባ
ክህ ፡ ጥጋብ ፡ ነፍቶኛልና ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡
ልጩህ" ፡ አለችው ። እሱም ፡ "ምነው ፡
አህዩት ፡ ያለንበት ፡ ቦታ ፡ በረሃ ፡ መሆኑን ፡
አያወቅሽ ፡ እንዴት ፡ ልጩህ ፡ ትያለሽ? ያ

ወዳጃችን ፡ አቶ ፡ ጅብ ፡ የሰማ ፡ እንደሆነ ፡ መበላታችን ፡ አይደለምን?” አላት ። አህ ዪት ፡ ግን ፡ “በፍጹም ፡ የማይሆን ፡ ነገር ፡ ነው ፡ በጣም ፡ ጠግቤያለሁና ፡ አንዴ ፡ መ ጮህ ፡ አለብኝ” ፡ ብላ ፡ በረዥሙ ፡ አናፋች።

አሁንም ፡ ከጨሌው ፡ ሣር ፡ ጥቂት ፡ ነጨት ፡ ነጨት ፡ አደረገችና ፡ “እንደገና፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ላናፋ” ፡ አለች ። ውሻም ፡ “እባክሽ ፡ ተዪ ፡ የቅድሙ ፡ ማሰሚያ ፡ የአ ሁኑ ፡ ማቅረቢያ ፡ ይሆናል” ፡ አላት ። እሷ፡ ግን ፡ እንደቀድሞዋ ፡“እምቢ” ፡ ብላ ፡ጩኸ ቷን ፡ አቀለጠችው ። ለካስ ፡ አቶ ፡ ጅብ ፡ የመጀመሪያውን ፡ ጩኸት ፡ ሰምቶ ፡ አቅጣ ጫው ፡ ጠፍቶት ፡ ይባዝን ፡ ኖሮ ፡ ሁለተ ኛው ፡ በተደገመ ፡ ጊዜ ፡ አቅጣጫውን ፡ አውቆ ፡ ሮጦ ፡ መጣ ።

አህዪትም ፡ ከሣሩ ፡ ነጫጨችና ፡ ሦስ ተኛ ፡ ጊዜ ፡ ውሻውን ፡ “ልጩህ” ፡ አለ ችው ። ውሻም ፡ “ተዪ ፡ አይሆንም ፡ ውር ድ ፡ ከራሴ ፡ ነው ፤ የመጀመሪያው ፡ መቀስ ቀሻ ፡ የሁለተኛው ፡ ማቅረቢያ ፡ የሦስተ ኛው ፡ ግን ፡ መበያ ፡ እንደሆነ ፡ አትጠራ ጠሪ ፡ ስለዚህ ፡ እንበላለንና ፡ እባክሽ ፡ ይቅ ርብሽ?” ቢላት ፡ “እምቢ” ፡ ብላ ፡ ጮኸች።

ጅቡም ፡ እቅርብ ፡ ኖሮ ፡ "እሆ" ፡ ብሎ ፡ ሆዷን ፡ ዘርክቶ ፡ ጣላት ። ቶሎ ፡ ቶሎም ፡ በልቶ ፡ በጠገበ ፡ ጊዜ ፡ መለስ ፡ ቢል ፡ ውሻን ፡ ጥቅልል ፡ ብሎ ፡ ተኝቶ ፡ አየውና ፡ "አንተ ፡ ደግሞ ፡ ምንድር ፡ ነህ?" ብሎ ፡ ጠየቀው ። ውሻም ፡ "እኔማ ፡ የጌታዬ ፡ ሥጋ ፡ ቤት ፡ ነኝ" ፡ አለው ። ጅብም ፡ "ብልት ፡ ማውጣትስ ፡ ከቻልክ ፡ እያወራረድህ ፡ አቅርብልኝ" ፡ አለውና ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ ቁጭ ፡ አለ ። ውሻም ፡ ወደ ፡ ሆድ ፡ ዕቃዋ ፡ ዘው ፡ ብሎ ፡ ቢገባ ፡ ልቧን ፡ አገኘው ። ርቦት ፡ ስለነበረም ፡ ዋጥ ፡ አደረጋት ። ጅብም ፡ ተጠራጠረና ፡ "አንተ ፡ ውሻ ፡ እስኪ ፡ ልቧን ፡ አምጣልኝ" ፡ አለው ።

ውሻም ፡ "ጌታዬ ፡ አህያዪቱ ፡ ልብ ፡ የላትም" ፡ አለው ። ጅብም ፡ "እንዴት ፡ ልብ ፡ የላትም" ፡ ቢለው ፡ አቶ ፡ ውሻ ፡ "ጌታዬ ፡ ምኝነዎትና ፡ ልብማ ፡ ቢኖራት ፡ ከዚህ ፡ ምን ፡ አመጣት?" ፡ አለው ፡ ይባላል ።

ጦጣና ፡ ተማሪ ።

በአንድ ፡ ገዳም ፡ አንድ ፡ ተማሪ ፡ ይኖር ፡ ነበር ። ይህም ፡ ተማሪ ፡ በዚያው ፡ ገዳም ፡ ቅኔ ፡ ይማር ፡ ነበር ። ትምህርቱን ፡ የሚቀጽለው ፡ ሌሊት ፡ ሌሊት ፡ ነበር ። ቀን ፡ ቀን ፡ ግን ፡ ሌሊት ፡ ሌሊት ፡ የተማረውን ፡ ቅኔ ፡ ለወደፊት ፡ እንዲረዳው ፡ በመቃ ፡ ብርዕ ፡ በብራና ፡ ላይ ፡ ከአንድ ፡ ትልቅ ፡ ወርካ ፡ ሥር ፡ ተቀምጦ ፡ ይጽፋል ። ሲጽፍ ፡ ቆይቶ ፡ ሲደክመው ፡ ቀለሙን ፡ ብርውንና ፡ ብራናውን ፡ ከዚያው ፡ ከወርካው ፡ ሥር ፡ ትቶ ፡ ምሳውንና ፡ እራቱን ፡ ለማግኘት ፡ ወደ ፡ መንደር ፡ ይሄዳል ። ምግቡን ፡ ቀፍፎ ፡ እስቲመለስ ፡ ድረስ ፡ የጻፈው ፡ ተበላሽቶ ፡ በብራናውም ፡ ላይ ፡ ተሞጫጭሮ ፡ ያገኘዋል ። ይህንንም ፡ የሚያደርግበት ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ አላወቀውም ። በዚህም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይበሳጭ ፡ ነበር ።

አንድ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ መንደር ፡ በመሄድ ፡ ፈንታ ፡ ከሩቅ ፡ ሆኖ ፡ ወርካውን ፡ ያይ ፡ ጀመር ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡ በወርካ ፡ ላይ ፡ ፍሬውን ፡ ስትበላ ፡ የምትውለው ፡ ጦጣ ፡ ከዛፍ ፡ ላይ ፡ ወርዳ ፡ በእርሱ ፡ ቦታ ፡

ስትቀመጥ ፡ አየ ። ወዲያውም ፡ በእርሱ ፡
እግር ፡ ተተክታ ፡ ትጽፍ ፡ ጀመር ።
እርሱም ፡ ጠላቱ ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ ስለ
አወቀ ፡ ማጥፊያ ፡ ዘዴ ፡ መፈለግ ፡ እንደአለ
በት ፡ አሰበ ። እንዲህም ፡ ሲል ፡ ዘዴ ፡
ፈጠረ ። "ይህች ፡ ጦጣ ፡ እንደኔ ፡ እጽፋ
ለሁ ፡ ብላ ፡ ነው ፡ የምታጠፋብኝ ። ባለፈ
ውም ፡ ሆነ ፡ በዛሬው ፡ ጥፋቷ ፡ ምንም ፡ አል
ላት ። ግን ፡ ቢለዋና ፡ የዶሮ ፡ ላባ ፡ ልፈ
ልግ" ፡ አለ ። ቢለዋውንና ፡ የዶሮ ፡ ላባው
ንም ፡ ፈልጎ ፡ አገኘ ። ዶሮ ፡ ላባውንና ፡ ቢለ
ዋውን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ እዚያ ፡ ቦታ ፡ ሄደ ።
እንደደረሰም ፡ ጽሕፈቱን ፡ ጻፈ ። ቆይቶም ፡
እንደደከመው ፡ ሰው ፡ ተንጠራራና ፡ ወደ
ላይ ፡ አየ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጦጣዋ ፡ ወደ ፡
እርሱ ፡ መመልከቷን ፡ አስተዋለ ።
ያን ፡ ዶሮ ፡ ላባ ፡ አነሣና ፡ አንገቱን ፡
ገዘገዘበት ። ጦጢቷም ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ሲ
ሠራ ፡ በማየቷ ፡ ገርሟት ፡ አተኩራ ፡ አየ
ችው ። እርሱም ፡ ላባውን ፡ አስቀመጠና ፡
ቢላዋውን ፡ አነሣና ፡ በደንደሱ ፡ በኩል ፡
አንገቱን ፡ በኃይል ፡ ገዘገዘበት ።
ጦጢት ፡ ዛሬ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ በማየቷ ፡
አለቅጥ ፡ ደስ ፡ አላት ፡ "ለመቼም ፡ እርሱ ፡

CamScanner

በሄደና ፡ እኔም ፡ እንደ ፡ እርሱ ፡ ባደረግሁ”፣ አለች ፡ በሆዷ ። እርሱ ፡ እንደዚህ ፡ ያደረገው ፡ አንገቱን ፡ እንዳይጎዳ ፡ በአንገቱ ፡ ዙሪያ ፡ የአንገት ፡ ልብስ ፡ ጠምጥሞ ፡ ነበር። ሰዓትም ፡ ደረሰና ፡ ወደ ፡ መንደር ፡ ሄደ ። ጦጢትም ፡ በፍጥነት ፡ ወርዳ ፡ ብርዕ ፡ አንስታ ፡ ጫር ፡ ጫር ፡ አደረገች ፡ ወዲያው ፡ ልክ ፡ እንደርሱ ፡ ዶሮ ፡ ላባውን ፡ አንሥታ፣ አንገቷን ፡ ገዘገዘችና ፡ አስቀመጠች ። ደግሞ ፡ ያን ፡ ቢለዋ ፡ አነሣችና ፡ ባዶ ፡ አንገቷን ፡ በደንደሱ ፡ በኩል ፡ ሳይሆን ፡ በስለቱ፡ በኩል ፡ በኃይል ፡ ብትገዘግዘው ፡ አንገቷን ፡ ቆርጣ ፡ ጣለችው ። እርሷም ፡ ወደቀች ። ወዲያውም ፡ ነፍሷ ፡ ወጣ ። ተማሪውም ፡ ሲመለስ ፡ ሞታ ፡ ስላገኛት ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ፎከረ ፡-

“ተሜ ፡ ተሚሻ ፤ እንቺን ፡ ለማጥፋት ፡ ሌላም ፡ ዘዴ ፡ አይሻ ።”

ሁለት ፡ ቆቆች ፡

ሶሪቴ ፡ የሚባል ፡ ቆቅና ፡ ሚስቱ ፡ በኑሯቸው ፡ እየተደሰቱ ፡ ተዋድደው ፡ በአንድ ፡

ደን ፡ ውስጥ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ሶሪቴም ፡ ከቤታቸው ፡ ራቅ ፡ ወዳለ ፡ ሥፍራ ፡ እየሄደ ፡ ለምግባቸው ፡ የሚሆነውን ፡ ማናቸውንም ፡ የምግብ ፡ ዓይነት ፡ ያመጣ ፡ ነበር ። ሚስቱም ፡ ከቤት ፡ ሆና ፡ ምግባቸውን ፡ በደንብ ፡ ታዘጋጅና ፡ ሶሪቴ ፡ ከሥራው ፡ ሲመለስ ፡ ምግቡን ፡ አቅርባ ፡ እየተጫዋወቱ ፡ አብረው ፡ ይበሉ ፡ ነበር ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ባልየው ፡ ለምግባቸው ፡ የሚሆን ፡ ጥሬ ፡ ለመፈለግ ፡ ወደ፡ አንድ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ወጣ ። ከዚያም ፡ እንደደረሰ ፡ ለሚስቱና ፡ ለእርሱ ፡ የሚሆን ፡ ምግብ ፡ እየጫረ ፡ ከአንድ ፡ አውድማ ፡ ላይ፡ ብዙ ፡ ለምግባቸው ፡ የሚሆን ፡ ጥራጥሬ ፡ አገኘ ። ከምግቡም ፡ ብዛትና ፡ ጣፋጭነት ፡ የተነሣ ፡ ተደስቶ ፡ ያማረውን ፡ ድምፁን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

“ይህን ፡ ጣፋጭ ፡ ምግብ ፡ ስሰጣት ፡
ለሚስቴ ፤
ጉሽ ፡ ትለኛለች ፡ ይረካል ፡ ሕይወቴ
እርሷም ፡ ከደስታ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ
ስትዘፍን ፡ ነበረች ፡ ስትል ፡ ነሣ ፡ ነሣ”

እንዲህም ፡ እያለ ፡ ሶሪቴ ፡ ሲዘምር ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ቆቅ ፡ ሰምቶት ፡ ምን ፡ እግኝ

ቶ፡ይሆን?ብሎ፡ወደ፡ሶሪቴ፡ዘንድ፡ቢሄድ፡ አውድማ፡ሲጭር፡አገኘው። ከዚያም፡ተናድዶ፡ "እኔ ፡ የምጭረውን ፡ አውድማ ፡ የምትጭርብኝ ፡ ለምንድር ፡ ነው?" ፡ አለና ፡ ሶሪቴን ተናንቆ ፡ ራስ-ራሱን ፡ በአፉ ፡ ኮርኩሞ ፡ ገደለው ።

የሟቹም ፡ ቆቅ ፡ ሚስት ፡ በተለመደው፡ ሰዓት ፡ ሳይመጣ ፡ ስለቀረ ፡ ሕይወቱ ፡ ያለ ፡ መስሏት ፡ ምሳውን ፡ አዘጋጅታ ፡ ወደ ፡ ወጣበት ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ይዛለት ፡ ወጣችና፡ "ሶሪቴ ፡ እንጀራ ፡ በቁና ፤ ውኃ ፡ በቅምጫና ፤ አምጥቻለሁና ፤ ቶሎ ፡ ና ፡ ቶሎ፡ ና።" እያለች ፡ ትጠራው ፡ ጀመር ።

ገዳዩም ፡ ቆቅ ፡ ይህን ፡ ሰማና ፡ "ሶሪቴ ፡ ሶሪቴ ፡ ሶሪቴ፡የት፡አሉ፤አውድማ ፡ሲጭሩ፡ ድፍት ፡ ሙትት ፡ አሉ ፤ እንግዲህ ፡ ቆቂቴ፡ እኔ ፡ ላግባሽ ፡አሉ።" ብሎ ፡ መለሰላት ።

ቆቂቴ ፡ መለሰችና ፡ "አንቱ ፡ ብታገቡኝ ፡ ምን ፡ ታበሉኛለሁ?" ፡ ምን ፡ ታጠጡኛለሁ?" ብላ ፡ ጠየቀችው ።

ቆቁም ፡ "እኔማ ፡ ባገባሽ ፡ ጥሩ ፡ ቤት ፡ ሠርቼ ፡ አውድማ ጫጭሬ ፡ ከሌላም ፡ ነጥቄ" ፡ አላት ።

ቆቂት ፡ ነገሩን ፡ ለወጥ ፡ አደረገችና ፡

"የሆነስ ፡ ሆነና ፡ አፍዎን ፡ ምን ፡ ሰነጣጠቀው" ፡ ብላ ፡ ጠየቀችው ።

ቆቁም ፡ "የቆቆችን ፡ ንጉሥ ፡ ጠፍ ፡ መሬት ፡ አልማ ፡ ተብዬ ፡ ሳለማ ፡ ነው ፡ የተሰነጣጠቀብኝ" ፡ አላት ።

ይህን ፡ መልስ ፡ ከሰማች ፡ በኋላ ፡ ቆቂት ፡ "አንድ ፡ ዓይንዎንስ ፡ ምን፡አጠፋብዎ?" ፡ ብላ ፡ ጠየቀችው ።

ቆቁም ፡ "ንጉሥ ፡ ስለሚወዱኝ ፡ ከእልፍኛቸው ፡ አስጠርተው ፡ ጠጅ ፡ ሲያጠጡኝ ፡ አንድ ፡ ተንኮለኛ ፡ እረኛ ፡ በእጁ ፡ ጠንቁሎ ፡ አጠፋው" ፡ አላት ።

ከዚያ ፡ ቆቂት ፡ "አንቱ ፡ ውሸታም ፤ እረኛ ፡ ደግሞ ፡ ምን ፡ ሊያደርግ ፡ ከንጉሥ ፡ እልፍኝ፡ ገብቶ፡ዓይንዎን፡አጠፋው? ደግሞስ፡ ቆቅ ፡ ከንጉሥ ፡ እልፍኝ ፡ ገብቶ ፡ ጠጅስ ፡ መቼ ፡ ጠጥቶ ፡ ያውቃልና ፡ ነው ፡ ተጋበዝሁ ፡ የሚሉት ፡እንዳንቱ፡ያለ፡ውሸታም፡ ባል ፡ አይሆነኝም ።" ብላው ፡ ወደ ፡ መኖሪያዋ ፡ ብርር ፡ አለች ።

ትልቁም ፡ ቆቅ ፡ ተናድዶ ፡ ተከተላት ። እርሷ ፡ ግን ፡ ጥቅጥቅ ፡ አለ ፡ ደን ፡ ውስጥ፡ ገብታ ፡ ተሸሸገች ። እርሱም ፡ ገብቶ ፡ ለመፈለግ ፡ ቢሞክር ፡ አቃተው ፡ ምክንያቱም ፡

ደኑ : ጥቅጥቅ : ያለ : ከመሆኑም : በላይ : ቆቁም : አንድ : ዓይን : ስለነበረ : አረጋግጦ ስለማያይ : ነው ። ይህ : ሁሉ : ሲሆን : የሰ ሪቱ : ሚስት : ከአንድ : የዛፍ : ሥር : ተጠ ግታ : አድፍጣ : ነበር ። በኋላም : አቅቶት : ሲመለስ : እርሷም : ወደ : መኖሪያዋ : ጫካ : እየተሹለከለከች : ሄደች ።

አመካኙተው : በሏት ።

አራዊቶች : አንድነት : ተሰብስበው : ምግብ : ፍለጋ : ሄዱ ። ምንም : ሳያገኙ : ለብዙ : ጊዜ : ተንከራተቱ : አንድ : ቀን : ከመካከላቸው : አንደኛው : አንድ : ሐሳብ : አቀረበላቸው ።

"ይህን : ያህል : ቀን : ምግብ : ሳናገኝ: በረሃብ : ተሰቃየን ። ከመካከላችን : አንድ : ትልቅ : ኃጢአት : የሠራ : ቢኖር : ነው : እንጂ : ምግብ : አናጣም : ነበር ። ስለዚህ : አሁን : እያንዳንዳችን : በየተራ : እየተነሣን የሠራነውን : ኃጢአት : እንናዘዝ" : አላቸው ።

ሁሉም : በነገሩ : ተስማምተውበት : ለፍርድ : ተቀመጡ ። በመጀመሪያ : አን

በሳ : እንዲህ : ሲል : ተናዘዘ ። "አንድ : ቀን : አጥር : የሰበረች : መሲና : አግኝቼ : በልቻለሁ ። ይህ : ኃጢአት : እንደሆነ : ፍረዱብኝ : አላቸው » ።

ጅብም : ተነሣና : "አንድ : ሽክም : ያቃታት : መጋገር : አግኝቼ : በልቻለሁ ። ይህም : ኃጢአት : እንደሆነ : ፍረዱብኝ :" አለ ።

ነብርም : ደግሞ : በተራው : ተነሣና : እንዲህ : አለ ።"አንድ : ቀን : አንድ : ወጠጤ : ፍየል : ከእረኛው : አምልጦ : ከጫካ : ውስጥ : ቅጠል : ሲቀነጣጥስ : አግኝቼ : በልቼዋለሁ ። ይህም : ከኃጢአት : ይቆጠር : እንደሆነ : ፍርዳችሁን : ልቀበል : ዝግጁ : ነኝ" : አለ ።

የቀሩትም : እንስሶች : በየተራቸው : እየተነሡ : ኃጢአታቸውን : ከተናዘዙ : በኋላ : ወይዘሮ : አህያ : በተራዋ : ተነሥታ : ትዘባርቅ : ጀመር ። እርሷም : "አንድ : ቀን ጌታዬ : እህል : ጭኖብኝ : ሲሄድ : በድንገት : ከሰው : ጋር : ተገናኝቶ : ቆሞ : ሲያወራ : ጥቂት : እልፍ : ብዬ : ሰርዶ : ነጭቻለሁ" : ብላ : ተናገረች ።

ዳኞቹም : ፍርዳቸውን : ሲሰጡ : "መሲ

ናዋ ፡ አጥር ፡ የሰበረች ፤ ፍየሉም ፡ ከእረ
ኞች ፡ ያመለጠ ፡ መጋዣዋ ፡ ሽክም ፡ ያቃ
ታት ፡ ከሆኑ ፡ ኃጢአተኞቹ ፡ እነርሱው ፡
ናቸው ፡ እናንተ ፡ ምንም ፡ ኃጢአት ፡ የለባ
ችሁም” ፡ ብለው ፡ የዳኝነት ፡ ፍርዳቸውን፡
ሰጡ ።

ነገር ፡ ግን ፡ የወይዘሮ ፡ አህያ ፡ ኃጢ
አት ፡ ልዩ ፡ ጥናትና ፡ ምርመራ ፡ ያስፈልገ
ዋል ፡ ብለው ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ሲመካከሩ ፡
ቆዩ ። በኋላም ፡ “ተነሥተሽ ፡ ጌታሽን ፡
ሳትጠብቂው ፡ ሄደሽ ፡ ሰርዶ ፡ ነጭተሽ ፡
ከበላሽማ ፡ ጥፋትሽ ፡ የበዛና ፡ የሠራሽው ፡
ኃጢአት ፡ ትልቅ ፡ ስለሆነ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡
ፈርደንብሻል” ፡ ብለው ፡ በኃጢአቷ ፡ አመ
ካኝተው ፡ የመጨረሻውን ፡ ፍርድ ፡ ስለ
ሰጡ ፡ ወዲያውኑ ፡ ወይዘሮ ፡ አህያን ፡ ዘነ
ጣጥለው ፡ እንደቅርጫ ፡ ሥጋ ፡ ተከፋፍ
ለው ፡ በሏት ።

“መምረጥ ፡ ነው ፡ እኩያ ፡ ደግሞም
መጠንቀቅ ፤
ጉዳት ፡ ያገኘዋል ፡ አቅሙን ፡ የማያ
ውቅ ።”

አንድ ፡ ዶሮና ፡ ቀበሮ ።

አንድ ፡ ቀን ፡ ቀበሮ ፡ ከጎሬዋ ፡ ወጥታ ፡ ለሽ
ርሽር ፡ ወደ ፡ መንደር ፡ መጣች ። እርሷም ፡
አንድ ፡ አውራ ፡ ዶሮ ፡ ከአጥር ፡ ላይ ፡ ወጥ
ቶ ፡ ኩኩሉ ፡ ሲል ፡ ሰምታ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡
ቀረበች ። እንዲህም ፡ ብላ ፡ ዶሮውን ፡ ጠየ
ቀችው ። “እንደምን ፡ ዋልህ ፡ አቶ ፡ ዶሮ?
ኩኩሉ ፡ እያልህ ፡ ስትሸልል ፡ ለሰማህ ፡
ድምፅህ ፡ በጣ ፡ ደስ ፡ ይላል ፤ ከሩቅ ፡
ሆኜ ፡ ስሰማው ፡ በጣም ፡ ግሩም ፡ ነው ።
አሁንም ፡ ቀረብ ፡ ብዬ ፡ ለመስማት ፡ ወደ ፡
አንተ ፡ መጣሁ ፤ እባክህን ፡ እስቲ ፡ ያንን ፡
ጥሩ ፡ ድምፅህን ፡ አንዴ ፡ አሰማኝ” ፡ አለ
ችው ።

አውራ ፡ ዶሮም ፡ በቀበሮ ፡ ንግግር ፡
ኩራት ፡ ተሰማው ። ወዲያውም ፡ ጎንበስ ፡
ቀና ፡ አለና ፡ ዓይኑን ፡ ጨፍኖ ፡ “ኩኩሉ”፡
አለ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የጨፈነውን ፡ ዓይኑን ፡
ሳይገልጥ ፡ ኩኩሉ ፡ ማለቱንም ፡ ሳይጨርስ፡
ቀበሮዋ ፡ ዘልላ ፡ ክንፍና ፡ ክንፉን ፡ ይዛው፡
ወደ ፡ ጎሬዋ ፡ ሮጠች ። እረኞች ፡ ቀበሮዋ ፡
ዶሮውን ፡ ይዛ ፡ ስትሮጥ ፡ አይተው ፡ ተከ
ታተሏት ። አውራ ፡ ዶሮው ፡ ብልጥ ፡ ነበ



ረና ፡ ለቀበሮዋ ፡ ምክር ፡ አስመስሎ ፡ “እረኞች ፡ ዶሮአችንን ፡ ወሰደች ፡፡ »እያሉ ፡ ይጮኻሉ ፡፡ ተከትለው ፡ እንዳይገድሉሽ ፡ የናንተን ፡ ዶሮ ፡ አይደለም ፡ ብለሽ ፡ ንገሪያቸው” ፡ አላት ፡፡ ሞኝ ፡ እንደመከሩት ፤ ቀበሮዋም ፡ የጠላት ፡ ምክር ፡ መሆኑን ፡ ረስታ ፡ ቆም ፡ አለችና ፡ እረኞቹን ፡ “የናንተ ዶሮ ፡ አይደለም ፡ የኔ ፡ ነው” ፡ አለች ፡፡ ቀበ

ሮዋ ፡ ይህን ፡ ስትናገር ፡ ዶሮው ፡ ከአፏ ፡ አመለጠ ፡፡ አውራ ፡ ዶሮው ፡ “ነፍሴ ፡ አውጭኝ” ፡ ብሎ ፡ እዛፍ ፡ ላይ ፡ ወጣና ፡ ተቀመጠ ፡፡ ቀበሮዋንም ፡ “አሁን ፡ ያንቺ ፡ አይደለሁም ፡፡ በዩ ፡ በሰላም ፡ ወደ ፡ ቤትሽ ፡ ሂጂ” ፡ አላት ፡፡

ቀበሮዋም ፡ ከእርሷ ፡ የሚያንስ ፡ አውራ ፡ ዶሮ ፡ ስለአታለላት ፡ በጣም ፡ ተናደደች ፡፡ ወደቤቷም ፡ ስትሄድ ፡ “አፌ ፡ ተቅለብልበሽ ፡ ባትናገሪ ፡ ኖሮ ፡ ዛሬ ፡ የምትበዪውን፡ አግኝተሽ ፡ አታጭም ፡ ነበር” ፡ እያለች ፡ ተፀፀተች ፡፡

የአንድ ፡ ፈላስፋ ፡ ምክር ፡፡

በአንድ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ የሚኖር ፡ በጣም ፡ ብልኅና ፡ አስተዋይ ፡ የሆነ ፡ አንድ፡ ሽማግሌ ፡ ፈላስፋ ፡ ነበር ፡፡ ይህ ፡ ፈላስፋ ፡ ችግረኞችን ፡ በማጽናናትና ፡ በቂ ፡ ምክር ፡ በመስጠት ፡ የታወቀ ፡ ስለነበር ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ችግሯን ፡ ልታዋየው ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሄደች ፡፡

ቤቱ ፡ ከመንደሩ ፡ ወጣ ፡ ብሎ ፡ በሚገኘው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አጠገብ ፡ ነው ። በግዙሪያው ፡ በድንጋይ ፡ ካብ ፡ ታጥሮ ፡ በግቢው ፡ የጌሾና ፡ የኮባ ፡ ተክል ፡ አምሮ ፡ ይታያል ። ግቢው ፡ ጸጥ ፡ ያለ ፡ ነው ። በውስጡም ፡ ሰው ፡ ያለ ፡ አይመስልም ። የቤቱ ፡ በር ፡ ግን ፡ ወለል ፡ ብሎ ፡ ተከፍቶ ፡ ይታያል ።

ሴትየዋ ፡ ወደ ፡ በሩ ፡ ጠጋ ፡ ብላ ፡ "ቤቶች ፡ እንደምን ፡ ዋላችሁ" ፡ አለችና ፡ ቆመች ፡ "እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ማነሽ? ግቢ" ፡ የሚል ፡ የሽማግሌ ፡ ድምፅ ፡ ሰምታ፡ ገባች ።

ፈላስፋው ፡ በግድግዳው ፡ ጥግ ፡ እመደቡ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ መጽሐፍ ፡ ያነባል ። ጸጉሩ ፡ ሽበት ፡ የበዛበት ፡ ጽሕሙ ፡ እደረቱ ፡ ድረስ ፡ የተንዠረገገ ፡ ነው ። ባይኑ ፡ ላይ ፡ (አድርጎት) ፡ የነበረውን ፡ መነጽር ፡ ወለቅ ፡ አድርጎ ፡ "እዚህ ፡ ዐረፍ ፡ በይ ፡ ልጄ ፡ ምን ፡ ሆነሻል? የተበሳጨሽ ፡ ትመስያለሽ" ፡ ሲል ፡ ጠየቃት ። "እውነትዎን ፡ ነው ፡ አባቴ ፡ በጣም ፡ ተበሳጭቻለሁ" ብላ ፡ መለሰችለት ። እሱም ፡ "በይ ፡ አሁን የተቸገርሽበትን ፡ ንገሪኝ" ፡ አላት ።

እሷም ፡ "እንደተጋባን ፡ ባሌ ፡ በጣም ፡ ይወደኝ ፡ ነበር ። በምሳ ፡ ሰዓትና ፡ ማታ ፡ ከሥራ ፡ መጥቶ ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ይመጣ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ቶሎ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ መምጣቱን ፡ ትቶ ፡ የትም ፡ ያመሻል ፡ የት ፡ ዋልህ? ወይም ፡ የት ፡ አመሸህ? ብዬ፡ ስጠይቀው ፡ ይቆጣኛል ። እንዲያውም፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በጥፊና ፡ በርግጫ ፡ ይመታኛል ።" ብላ ፡ ነገረችው ።

ፈላስፋው ፡ ችግርዋን ፡ ካደመጠ ፡ በኋላ ፡ "አይዞሽ ፡ ግድየለሽም ፡ ችግርሽን፡ አስወግድልሻለሁ ። ግን ፡ መጀመሪያ ፡ የዱር ፡ አንበሳ ፡ ፈልገሽ ፡ ከጋማው ፡ ጥቂት ቆርጠሽ ፡ ማምጣት ፡ አለብሽ" ፡ አላት ። ሴትየዋም ፡ ያንበሳውን ፡ ጋማ ፡ በብልኀት፡ ቆርጣ ፡ ለማምጣት ፡ ዘዴ ፡ ፈለገች ።

አንድ ፡ ቀን ፡ በግ ፡ አሳርዳ ፡ አንበሶች፡ ወደሚገኙበት ፡ ሥፍራ ፡ አንድ ፡ እግር ፡ ሥጋ ፡ ይዛ ፡ ሄደች ። እዚያም ፡ እንደደረሰች ፡ አንድ ፡ አንበሳ ፡ እቋጥኝ ፡ ሥር ፡ ተኝቶ ፡ አየች ። ከእንቅልፉ ፡ እስኪነቃ ፡ ድረስ ፡ ቆማ ፡ ጠበቀችው ። አንበሳውም ፡ እንደነቃ ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ሲያዛጋ ፡ ሴትየዋን፡ አያት ። እሷም ፡ ሥጋውን ፡ ጣለችለትና ፡

ወደ ፡ ቤቷ ፡ ተመለሰች ። በማግሥቱም ፡ ሥጋ ፡ ይዛ ፡ ሄደች ። ከፊተኛው ፡ ትንሽ ፡ ቀረብ ፡ ብላ ፡ ጣለችለት ። በየቀኑ ፡ እንዲህ ፡ እየተጠጋች ፡ ስትጥልለት ፡ ቆይታ ፡ በመጨረሻ ፡ በጣም ፡ ተጠግታ ፡ ሥጋውን ፡ ሰጥታው ፡ ቆመች ። አንበሳው ፡ ሥጋውን ፡ ጨርሶ ፡ በላና ፡ ማንቀላፋት ፡ ጀመረ ። መተኛቱን ፡ ካረጋገጠች ፡ በኋላ ፡ በያዘችው ፡ መቀስ ፡ ከጋማው ፡ ትንሽ ፡ ቆርጣ ፡ እየተገላመጠች ፡ ወደ ፡ ቤቷ ፡ ተመለሰች ።

ያንበሳውን ፡ ጋማ ፡ ይዛ ፡ እፈላስፋው ፡ ዘንድ ፡ ሄደችና ፡ እንድታመጣ ፡ የታዘዘችውን ፡ አቀረበች ። ፈላስፋውም ፡ ተገርሞ ፡ "ከአንበሳው ፡ ጋማ ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ አድርገሽ ፡ ቆረጥሽው?" ፡ ብሎ ፡ ጠየቃት ። ሴትየዋም ፡ ያደረገችውን ፡ ሁሉ ፡ ነገረችው ። ፈላስፋው ፡ ሴትየዋ ፡ ባደረገችው ፡ ሥራ ፡ እየተገረመ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መከራት ። "አንበሳን ፡ የሚያህል ፡ አደገኛ ፡ አውሬ ፡ ጠባዩን ፡ አውቀሽ ፡ ጋማውን ፡ እስከመቁረጥ ፡ ድረስ ፡ የተላመድሽው ፡ እንዴት ፡ የባልሽን ፡ ጠባይ ፡ ማወቅ ፡ ያቅትሻል? በይ ፡ ባልሽ ፡ እሥራ ፡ ውሎ ፡ ሲመለስ ፡ እንደምን ፡ ዋልህልኝ ፡ ምን ፡ ላድርግልህ ፡ እያልሽ ፡ በለስላሳ ፡ ቃል ፡ አነጋግሪው ። ደክሞትም ፡ እንደሆን ፡ የሚያስፈልገውን ፡ እያደረግሽለት ፡ ጥሩ ፡ ዕረፍት ፡ እንዲኖረው ፡ አድርጊ ። የኑሮ ፡ ጓድሽ ፡ ስለሆነ ፡ ፍቅርሽን ፡ አትንፈጊው" ።

እሷም ፡ ስሕተቱ ፡ የራስዋ ፡ መሆኑን ፡ ተረድታ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የፈላስፋውን ፡ ምክር ፡ ተከትላ ፡ ለመኖር ፡ ቆርጣ ፡ ወደ ፡ ቤቷ ፡ ተመለሰች ። እንደ ፡ ተመከረችውም ፡ እያደረገች ፡ ከባልዋ ፡ ጋር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በደስታ ፡ ለመኖር ፡ ቻለች ።

ዋጋው የኢ.ት. $0.20

CamScanner